<<ሃይማኖት መሰረት ናት የቀሩት ግድግዳና ጣራ ናቸው::>>ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ

ምዕራፍ አንድ

ትምህርተ ሃይማኖት

<<ከሁሉ አስቀስሞ የሃይማኖትን ትምህርት መማር ይገባል>>318ቱ ሊቃውንት

<<ሃይማኖት መሰረት ምግባር ህንፃ ነውና >>1ኛቆሮ 3÷10

1.1 ትምህርተ ሃይማኖት መግቢያ

❖ **የሃይማኖት ትርጉም (ሃይማኖት ማለት ምን ማለት ነው)**

የሃይማኖት ትርጉምን በሁለት ከፍሎ ማየት ይችላል

❖ **የመዝገብ ቃላት ትርጉም**

❖ ሃይማኖት ቃሉ ‹‹ሃይመነ፣ አመነ ›› ከሚለው የግዕዝ ግሰ የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም ፡ ማመን ፡ መታመን፡ ተአማኒነት ማለት ነው::

➢ **ማመን** ፡ሰንል ‹‹ይህቺ አለም አሰገኚ ፈጣሪ መጋቢ የሆነ አለምን ከመፍጠሩ በፊት የነበረ አለምንም አሳልፎ የሚኖር ዘላለማዊ የሆነ አንድ እግዚአብሔር አምላክ አለ ብሎ ማመን

➢ **መታመን**፡- ያመኑትን ነገር መመሰከር እና ላመኑት ነገር መገዛት

ሮሜ 10÷9 <<ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደሆነ **በአፍህ ብትመሰክር...>>** መታመንን

➢ **ተአማኒነት** ፡-ያመኑት ነገር ያለምንም ጥርጥር የምፈልገውን ነገር ይደርግልኛልብሎ ማመን (ተሰፋ ማድረግ)

❖ **ምስጢራዊነቱ ትርጉም (የሃይማኖት መግላጫዎች)**

❖ ሃይማኖት ዝም ብለን የምንቀበለው ነው::

❖ ዝም ብለን የምንቀበለው ነው ስንል

ሃይማኖት ወይም እምነት ከስሜት በላይ ነው በዓይነሰሥጋ ታይቶ ለሚያየው በእጅ የማይዳሰሰው አምላክ አለ ብሎ ማመንን የተመለከተነው::

❖ በሳይንስ ለማመን ማየት ይቀድማል::

➢ ኤፌ 4÷13 በማመንና በማወቅ

❖ የእግዚአብሔር ህልውና በስሜት ህዋሳችን የማንረዳው ስለሆነ ነው::

❖ ሃይማኖት በተሰፋ የምንረዳው ነው ስንል

ዕብ 11÷1፡-እምነትም (ሃይማኖት)ተሰፋ ስለምናደረገው ነገር የሚያሰረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያሰረዳ ነው::

❖ ይህ ማለት ስለዘላለማዊ ሕይወት ስለመንግሰት ሰማያት በአይናችን አይተን በእጃችን ዳሰን በስሜት ህዋሶቻችን መርምርን የምንናገርው የምንመሰክረው ሳይሆን በተሰፋ አምነን የምንናገረው ነው::

❖ ሃይማኖት የማናየውን የምናይበት ረቂቅ መሳሪያ ነው::

2ቆሮ 12÷2-7 ቅዱስ ጳውሎስ ሶስተኛ ሰማይ ድረስ የተነጠቀው

ዕብ 11÷1-7 የማናየውን ነገር የምናይበት የሚያሰረዳው

❖ ሃይማኖት በስራ የምንተረጉመው ነው:: አብርሃም (አበ ብዙኃን)

- ሃይማኖት በፍቅር የተገለጠ ነው ። **ዮሐ 3፥16**
- ሃይማኖት እግዚአብሔርን ደስ የምናሰኝበት መንገድ ነው ።
  ማቴ 22፥37 ዕብ 11፥5-6 ያለ እምነት (ሃይማኖት) እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም።
  ዕብ 12፥28-29 1ጴጥ2፥1-5
- ሃይማኖት፡-በእግዚአብሔር መገለጥ ላይ የተመሰረተ ነው።
  1ኛ ጢሞ 3፡17

ሃይማኖት እንዴትና መቼ ተጀመረ?

- ሃይማኖት የተጀመረው ቅዱሳን መለዕክት እንደተፈጠሩ ነው።
- **ሀልወተእግዚአብሔርእንዴት እናውቃለን**
  የፈጣሪንመኖር እንዴት እንናውቃለን?

የሰው ልጅ በተፍጥሮ በተሰጠው እውቀት አእምሮ ፈጣሪውን የማመን ዝንባሌ ቢኖረውም የሰው እውቀት እጅግ ውስን በመሆኑ እግዚአብሔር ካልገለጸለት በስተቀር በልዩ ልዩ መንገድ በራሱ ተመረምሮ ማወቅ አይችልም።እግዚአብሔር ግን በወደደው መልኩ ሀልውናውን(አኗኗሩን) ለፍጥረታት የሚገልጥባቸው ነገሮች የሚከተሉት ናቸው።

1በሥነፍጥረት /የፍጥረት ሥነ ሥርዓትና አሠራር/

መዝ 18፥1**ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ የሰማይም ጠፈር የእጁን ስራ ያወራል**

ሮሜ 1፥20-21 **የማይታው ባሕርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከአለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሰሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና።**

መ.ኢዩ 12፥7-9 **አሁን ግን እንስሶችን ጠይቅ ይነግሩህምል...የእግዚአብሔር እጅ ይህንን እንዳደረገ**

ምሳሌ ፡- አበ ብዙሃን አብርሃም

በአጠቃላይ የማይለውጥና የማይዛባ የሥነፍጥረት ሥርዓት ያለው ዓለም ለእግዚአብሔር መኖርምስክር ነው።

2የህሊና ምስክርነት

- **ሕሊና ማለት** በሰውነት ውስጥ የሚገኝግብረ ገባዊ የሰሜት አካል ነው።

ሮሜ 2፥14-15 ...ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው ሃሳባቸውም እርስ በእርስ ሲካሰስ

3 የሰው ልጅ የተፍጥሮ ዝንባሌ

- በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ያሉ የሰው ልጆች በሙሉ በአምልኮት‌ሥርዓታቸው እና በሚያመልኩት ነገር ይለያይ እንጂ አምላክ መኖሩን ያምናሉ ስለዚህ ሰው የእግዚአብሔርን
  መኖር የሚያምነው የሃይማኖት መድሐፍትን አንብቦ ብቻ ሳይሆን የተፍጥሮ ስሜት ወይም ዝንባሌው ስለ ሚያሰገድደው ጭምሮ ነው።

ሐዋ 17፡22-34 ቅድስ ጳውሎስ በአቴና ከተማ ውስጥ በሚገኘው ኦርዮሰፈጎስ በተባለ የአምልኮ ቤት ለማይታወቅ አምላክ ተብሎ ተጽፎ ያገኘውን ፅሑፍ መነሻ አድርጎ የክርስትና እምነትን (ሃይማኖት)በመስበክ ብዙዎችን ለማሳመን የበቃው

4፡-በመግቦቱ

5:-የቃለ እግዚአብሔር የታሪክ ምስክርነት

አሰማተ መለኮት /የአምላክ ሰሞች/

1 **እግዚአብሔር** ፦ እግዚ-ጌታ፣አብ-አባት ፣ሔር-ቸር መሐሪ ሲሆን ጌታ ብሎ ወልድን አባት ብሎ አብንሔር ብሎ መንፈስ ቅዱስን ይገልጽልናል። በሌላ መልኩ እግዚኢ ጌታ ፣ብሔር ሁሉ ስለዚህ እግዚአብሔር የሁሉ ጌታ ተብሎ ይተረጎማል

2 **ኤል** የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን ኃያል አምላክ ማለት ነው።

3 **ኤልሻዳይ** የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን ሁሉን ቻይ ማለት ነው

4 **አዶናይ** ጌታ ገዢ ማለጽ ነው አልፋና ኦሜጋ ራ.ዮሐ 1-8

5 **ያህዌ** ያለና የሚኖር ማለት ነው

የእግዚአብሔር ባህርያት

1 **መንፈስ ነው፡-ከውሃ-እሳት-ነፍስ-መላዕክት-ከመላዕክት-ሃሳባችው ትረቃለች የእግዚአብሔር መንፈስ ደግሞ ከእነዚህ ሁሉ የረቀቀ ነው**

2 **ዘላለማዊ ነው**

3**ሁሉን ቻይ ነው (ከጎሌ ኩሉ)**

4**በሁሉ ሙሉ ነው (ሙልዕ በኩሉ)**

5**ሁሉን አዋቂ ነው**

6**ምንም እረዳት አያሰፈልገውም**

7**ቅዱስ ነው**

8 **ፃድቅ - እውነተኛ**

ሥነ ፍጥረት

- ***ሥነ-ፍጥረት ማለት ያማረ የተዋበ ፍጥረት ማለት ነው።***
  - ***የተሰማማ ሥነ ፍጥረት ማለት ነው።***

ዘፍ1÷3፡- ‹‹እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም እንደሆነ አየ››

- በአጠቃላይ የሥነፍጥረት ትምህርት እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት የፈጠረበትን ሥርዓት የምንማርበት ትምህርት ነው።
    - **የሥነ ፍጥረት ትምህርት መማር ለምን ያስፈልጋል?**

1. **የሕይወትን አላማ ለመረዳት**
    - ✓ ሰውንና መላዕክትን ስሙን ለመቀደስ ክብሩንም ለመውረስ
    - ✓ የተቀሩት ለአንክሮ ለተዘክሮ ለምግበ ስጋና ለምግበ ነፍስ

    } በአጭሩ ግን የፍቅሩ መገለጫዎች ናቸው።

2. **ሥነ-ፍጥረት እግዚአብሔርን ያሳውቃል**
    - ➢ ሥነ-ፍጥረት መኖሩን ብቻ ሳይሆን ባሕርይውንም ያስተምሩናል።

    በተለይ ስለ ሰው አፈጣጠርና ባሕርይ ማወቅ ምስጢር ሥጋዌንና ምስጢረ ሥላሴን ለመረዳት ጠቃሚ እንደሆነ ወደፊት ባሉት ክፍሎች የምናየው ይሆናል።

3. **በሥነ-ፍጥረት ትምህርት ሰውና መላዕክት ከፍጥረታት ተለይቶ ያላቸውን ክብር እናውቃለን።**
    - ➢ **እግዚአብሔር አምላክ ሥነ-ፍጥረቱን የፈጠረበት መንገድ**
        1. **እም ኀበ አልቦ ኀበ ቦ (ካለመኖር ወደ መኖር) (ሐዲስ ተፈጥሮ፣ ጥንተ ተፈጥሮ ይባላል)**
        2. **ግብር እምግብር**
    - ➢ **ሥነ-ፍጥረት የተገኙበት መንገድ**
        1. **በኂልዮ (በማሰብ) (በዝምታ፣ በአርምሞ)**
        2. **በነበብ (በመናገር)**
        3. **በገቢር (በመስራት)**

የስድስቱ ቀን ፍጥረታት

1. **የእለተ እሑድ ፍጥረታት**
    - ➢ የእለተ እሑድ ፍጥረታት በአጠቃላይ ካለመኖር ወደመኖር የተገኙ (የተፈጠሩ) ናቸው።
    - ➢ በዚህ እለት 8 ፍጥረታትን ፈጥሯል
        - አራቱ ባሕሪያተ ስጋ (ነፋስ፣ እሳት፣ መሬት፣ ውኃ)
        - ብርሃን
        - ጨለማ
        - ሰባቱ ሰማያት
        - መላዕክት
        - ጽርሐ፣ አርያም
        - መንበረ፣ መንግስት
        - ሰማይ፣ ውዱድ
        - ኢየሩሳሌም ሰማያዊ
        - ኢዮር
        - ራማ
        - ኤረር

        } የመላዕክት ከተማ (አለመ መለዕክት የመላዕክት ሀገር)

    - ➢ መላዕክት - በከተማ 10 - በኢዮር - 4
      - በራማ - 3
      - በኤረር - 3
    - ➢ በነገድ 100 - አድርጎ አስፍሯቸዋል

2. የእለተ ሰኑይ (ሰኞ) ፍጥረታት

- በዚህ እለት አንድ ፍጥረት ፈጠረ
- የዚህ እለት ፍጥረት ግብር እምግብር ። ከተገኘ ነገር ነው
- ከምድር እስከ ኤረር መልቶ የነበረውን ውኃ ለሦስት ከፈለው
    - በአየር ላይ አርግቶ **ጠፈር**አለው።
    - ከጠፈር በላይ የቀረውን ውሃ **ሀኖስ**
    - ከጠፈር በታች ያለውን ውሃ **ውቅያኖስ** ብሎጠራው

3. የእለተ ሰሉስ (ማክሰኞ) ፍጥረት

- በዚህ እለት ሶስት ፍጥረታትን ፈጥሯል
    - በእጅ የሚለቀሙ አትክልትን
    - በማጭድ የሚታጨድ አዝርዕት
    - በምሳር (በመጥረቢያ) የሚቆረጡ ዛፎች (እፅዋት)

4. የእለተ ረቡዕ ፍጥረታት

- በዚህ እለት ሶስት ፍጥረታን ፈጥሯል።
- በዚህ እለት እለተ እሑድ ተፈጥሮ **የነበረውን ብርሃን ወደ ሶስት ቅርፅ ቀይሮታል** አስቀምጦአል (ብርሃን ይሁን) ዘፍ1÷14-16
    - ፀሐይ
    - ጨረቃ
    - ከዋክብት

5. የእለተ ሐሙስ ፍጥረታት

- በዚህ እለት ሶስት ፍጥረታትን ፈጥሯል
    - ከውሃ ውስጥ የሚኖሩ
        - በደረታቸው የሚሳቡ
        - በእግራቸው የሚራመዱ (የሚሽከረከሩ)
        - በክንፋቸው የሚበሩ

6. የእለተ አርብ ስነ ፍጥረት

- **በዚህ እለት አራት ፍጥረታትን ፈጠረ**
    - በየብስ (መሬት) ላይ የሚኖሩ (በዓይነት)
        - በደረታቸው የሚሳቡ እንስሳት } እንስሳት
        - በእግራቸው የሚራመዱ } አራዊት
        - በክንፋቸው የሚበሩ (በእንቅስቃሴ) } አእዋፍ
- **የመጨረሻው የእለተ አርብ አራተኛው ፍጥረት የሰው ልጅ**
    - ለሰው የሚያስፈልገውንከፈጣረበኃላ
    - ሰውን በመልካቸው አምሳል ፈጥረውታል(ሥላሴ)።

7. የሰው ልጅ አፈጣጠር ከአራቱ ባህሪያቱ ስጋ እና ከሶስቱ ባህሪያተ ነፍስ

- የመጀመሪያው ሰው አዳምን የ30 ዓመት ጎልማሳ አድርገው በማዕከለምድር (በምድር መካከል በቀራንዮ ፈጠሩት)
- አራቱ ባህሪያ ስጋ - ከእሳት፣ ከመሬት፣ ከነፍስ፣ ከውኃ
- ሦስቱ ባህሪያተ ነፍስ - ነባቢነት፣ ሕያውነት፣ ልባዊነት
    - ልባዊነት - አዋቂነት
    - በሕያውነቷ - ዘላለማዊነትን

- በነባቢነት - ተናጋሪነት
- በሰባተኛው ቀን እግዚአብሔር ከሥራው ሁሉ አረፈ።

አዕማደ ምስጢር

- **አዕማደ ምስጢር የምንላቸው በቁጥር 5 ናቸው።**
  1. ምስጢረ ሥላሴ
  2. ምስጢረ ሥጋዌ
  3. ምስጢረ ጥምቀት
  4. ምስጢረ ቁርባን
  5. ምስጢረ ትንሳኤ መታን

ለምነ አምስት ሆኑ?

- **1 ቆሮ 14÷19፡- ‹‹ ከሁላችሁ ይልቅ በልሳኖች እናገራለሁ እግዚአብሔርንም አመሰግናለሁ ነገር ግን ሌሎችን ደግ አስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ››**
- **አዕማድ ማለት ምን ማለት ነው?**
  - **አዕማድ** የሚለው ቃል አምድ ከሚለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ሲሆን በሁለት መንገድ ተርጉመን እናየዋለን
  - **አዕማድ (አምድ)** ለቤት ከሆነ **ምሰሶ** ማለት ነው። ምሰሶ ቤትን ተሸክሞ እንደሚያጸናው ሁሉ እነዚህ ምስጢራትም አንድን ክርስቲያን በክህደት በጥርጥር እንዳይወደቅ አጽንተው ይደግፉታል፡ ፡
  - **አእማድ (አምድ)** ለጽሕፈት ሲሆን ደግሞ ለገጽ ስፋት መክፈያነት ያገለግላል (መመጠኛነት)። አምድ ጽሕፈት እንደሚመጥን ሁሉ እነዚህ ምስጢራት ባህርየ ሥላሴን ከመጠን አልፈን(ከአቅማችን በላይ) እንዳንመረምር ይገድቡናል።
- እነዚህ ምስጢራት አእማድ መባላቸው ለምንድን ነው ቢሉ አምድ /ምሰሶ/ ቤትን እንዲያጸናው እነዚህም የምእመናን ልብ ያጸናሉና ነው።
  - ምሰሶ የሌለው ቤት እንደሚወድቅ ሁሉ
- **ምስጢር ማለት ምን ማለት ነው?**
  - ምስጢር ማለት ስውር ድብቅ፣ ሸሽግ፣ ለልብ ወዳጅ ብቻ የሚነገር ማለት ነው።

እነዚህን ምስጢራት ቅድስት ቤተክርስቲያናችን ምስጢር ስትላቸው ለልብ ወዳጆቿ ለሆኑት ለሚያምኑ ለክርስቲያኖች ብቻ ሰውራ፣ ሸሽጋ የምትነግራቸው ለማያምኑት የተደበቀ ስለሆነ ነው።

- ምስጢር መባላቸው በአይነ ስጋ ስለማይታየው በእጅ ስለማይዳሰሰው ዘለአለማዊ አምላክ አንድነት፣ ሶስትነት ስጋ ለመዋሐዱ፣ ስለዳግም ምፅአቱ ስለሚናገሩ ነው። ምክንያቱም እነዚህን ምስጢራት በስጋዊ ጥበብ ውስን በሆነው በሰው አእምሮ ተመራምረን አንደርስባቸውምና ነው።
- **እነዚህ ምስጢራት ምስጢር መባላቸው ለምንድን ነው ቢሉ?**
  - የምናውቀው የምስጢራቱ ባለቤት የሆነው እግዚአብሔር የገለጠልንን ያህል በመሆኑ ነው።
  - በስጋዊ ጥበብ ምርምር እና እውቀት መረዳት የምንችላቸው ባለመሆኑ ነው።
  - ከእነዚህ ምስጢራት አስቀድመን ልንማር የሚገባው ምስጢር ምስጢረ ሥላሴን እንደሆነ አባቶቻችን እንዲህ በማለት ያስተምራሉ
  - **ቅዱስ ቁርሎስ :- ‹‹መቅደመ ኵሉ ንስብክ ሥላሴ ስሩየ››**

‹‹ከሁሉ አስቀድመን የሥላሴን አንድነትና ሶስትነት እናስተምራለን››

ምዕራፍ ሁለት
ምስጢረ ሥላሴ

- ሥላሴ፡- የሚለው ቃል ‹‹ሰለሰ (ሶስት አደረገ)›› ከሚለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ሲሆን ሶስትነት ማለት ነው፡፡
- ሦስትነት እና አንድነት
  - አጠቃላይ የምስጢረ ሥላሴ ትምህርት የሥላሴን (የእግዚአብሔርን) አንድነትና ሶስትነት የምንማርበት ትምህርት ነው፡፡
- አባ ሕርያቆስ በቅዳሴ ማርያም ትምህርቱ
  ‹‹እንዲህ እናምናለን እንዲህም እንታመናለን አንድነትን ሳንለይ የተለየ እንዳይሆን የተቀላቀለ እንዳይሆን እንለይ፣ እንደ አብርሃም ...
  - ❖ የእግዚአብሔር (የሥላሴ) አንድነትና ሦስትነትን በምን በምንድነው?
- **የሥላሴ አንድነት**
  - በባሕርይ በመፍጠር
  - በስልጣን በአገዛዝ
  - በመለኮት በፈቃድ .....
  - በህልውና (በአኗኗር)

❖ **የሥላሴ የባሕርይ አንድነት እንዴት ነው ቢሉ**

- ሁሉን በማወቅ፣ ሁሉን በማድረግ፣ ሁሉን በመቻል አንድ ናቸው፡፡

ዮሐ16÷15፡- ‹‹ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው››

- **የሥላሴ የሕልውና አንድነት እንዴት ነው ቢሉ**
  - **በቃልነት በልብነት በእስትንፋስነት ዮሐ8÷16-19፣ ዮሐ8÷29÷ዮሐ11÷4**
- **ዮሐ 14÷10፡- ‹‹እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለሁ አታምንምን?››**

- **የሥላሴ የመለኮት አንድነት እንዴት ነው ቢሉ**
  - መለኮት፡- መለኮት (ገዛ) ከሚለው የግዕዝ ግስ የተገኘ ሲሆን አገዛዝ ማለት
  - አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ይህን አለም ፈጥሮ በመመገብ በማስተዳደር በመግዛት በኋላም በማሳለፍ የሚያልፉትንደግም በማጽናት አንድ ናቸውና ነው፡፡

ዘፍ18÷1-4፡- ‹‹ ...አቤቱ በፊትህ ሞገስን አግኝቼ እንደሆነ ባሪያህን አትለፈኝ...››

- **የሥላሴ የፈቃድ አንድነት እንዴት ነው ቢሉ**
  - ሥላሴ ይህንን ዓለም በጥንተ ተፈጥሮ (በሐዲስ ተፈጥሮ) ሲፈጥሩ (ካለመኖር ወደመኖር ሲያመጡ) ኋላም (ወደፊትም) ይህን ዓለም ሲያሳልፉ (ከመኖር ወዳለመኖር ሲያሳልፉ) በአንድ ፈቃድ ነው፡፡

ዘፍ 1÷26፡- ‹‹እግዚአብሔርም አለ ሰውን በመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር››አለ፡፡

- እንፍጠር የሚለው ቃል የፈቃድ አንድነታቸውን ያሳያል፡፡

ዮሐ 10÷30፡- ‹‹እኔና አብ አንድ ነን››

የሥላሴ ሦስትነት

- ✓ በስም
- ✓ በአካል
- ✓ በግብር
- ✓ በኩነት

➢ **የሥላሴ የስም ሶስትነት እንዴት ነው ቢሉ**

- አብ፣ ወልድ፣ መንፈስቅዱስ

❖ **የሥላሴ የአካል ሦስትነት እንዴት ነው ቢሉ**

- **አካል**፡- ማለት ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍር ድረስ ያለውን ነው
- **ገፅ**፡- አንድን ሰው (አካል) ከሌላው ለይተን የምናውቅበት መገለጫ መታወቂያ ማለት ነው፡፡
- ***መልክ***፡- በአካላት ላይ ያሉ የአካል ክፍሎች አይን፣ እጅ፣ እግር ወዘተ... ናቸው፡፡

➢ አብ ፍፁም አካል ፍፁም መልክ ፍፁም ገጽ አለው፡፡

➢ ወልድ ፍፁም አካል ፍፁም ገጽ ፍፁም መልክ አለው፡፡

➢ መንፈስ ቅዱስ ፍፁም አካል ፍፁም ገጽ ፍፁም መልክ አለው፡፡

❖ **የሥላሴ የግብር ሶስትነት እንዴት ነው ቢሉ**

➢ አብ ፡- ወልድን ይወልዳል መንፈስቅዱስን ያሰርፃል አብ አስገኝ መሠረት ሥለመሆኑ እንገዲህ የአብ ግብሩ መውለድ ማሥረጽ መውለድና ማስረጽ አንድ ወገን ሆኖ አብ አስገኝ የሁሉ መገኛና ምንጭ እንደሆነ እናስተውላለን አብ አይወለድም አይሠርጽም እርሱ ወላዲ አስራጺነው፡፡ እርሱ ሁል ጊዜ በአስገኝነቱ የጸና ነው፡፡ አብ አባት የሌለው አባት አስገኚ የሌለው አስገኚ ሆኖ ለዘላለም ይኖራል፡፡ቅዱስ ኪራኮስ እንደጻፉ አብ አልተወለደም ማንም ከማን አልተገኘምና መገኘቱም ከሌላ አካል ከሌላ ባሕሪ አይደለምና እርሱ በቻ መገኛ እንጂ በማለት የአብንግብር ማለት የአባትነትን የአስገኝነትን አብራርቶልናል፡፡ሃ.አበው ገጽ 397 ዮሐ8÷42 ዮሐ15÷26

➢ ወልድ፡- ከአብ ይወለዳል (መወለድ)አብ ወልድን ወለደው ማለት ከአካሉ ከባህሪው አስገኚ ማለት ነው፡፡አብ ወልድን በቃል አምሳል ወለደው ሥርወ ሃይማኖት 1960ዓ.ም ገጽ40-45 ወልድ በተለየ አካሉ ተወላዲ ነው እንጂ እንደ አብ አይወልድም አያሠርፅም እንደ መንፈስ ቅዱስም አይሰርፅም፡፡

ለምሣሌ፡- ወልድ ከአብ ተወለደ ማለት ከአካሉ የሰው ነፍስ ልብነቷ ቃልነቷን እንደሚየስገኝ ማለት ነው፡፡ ወለድ አብን አህሎ አብን መስሎ ከአብ ተገኝ ማለት ነው፡፡

➢ መንፈስ ቅዱስ ከአብ ይሰራፀል፡- (መስረፅ መውጣት) አብ መንፈስ ቅዱስን አሰረፀው ማለት ከአካሉ ከባህሪው አስገኚ ማለት ነው፡፡እንግዲህ አብ መንፈስ ቅዱስን በእስትንፋስ አምሳል አሠረፀው ..አወጣው አስገኘው ማለት ነው፡፡ሥርወ ሃይማኖት 1960ዓ.ም ገጽ40-45 መንፈስ ቅዱስ በተለየ አካሉ ሠራዒ ነው አንጂ እንደ አብ አይወልድም አያሠርፅም እንደ ወልድም አይወለድም ፡፡

ለምሣሌ፡-የነፍስ ልብነቷ እስትንፋስነቷን (ሕይወቷን) እንዳስገኘው ነው፡፡መንፈስ ቅዱስም ከአብ ሠረፀ ማለት አብን አህሎ መስሎ ከአብ ተገኘ ማለት ነው፡፡

❖ **የሥላሴ የኩነት ሶስትነት እንዴት ነው ቢሉ**

- ከዊነ ልብ (ልብ መሆን) - አብ
- ከዊነ ቃል (ቃል መሆን) - ወልድ
- ከዊነ እስትንፋስ (እስትንፋስ መሆን) - መንፈስ ቅዱስ

ለሥላሴ አንድነትና ሦስትነት የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃዎች

በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት

- ዘፍ1÷26‹‹እግዚአብሔርም አለሰውን እንደመልካችን እንደምሳሌያችን እንፍጠር›› አለ፡፡
- ዘፍ2÷18 ‹‹እግዚአብሔር አምላክም አለ፡፡ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፣ የሚመቸውን እረዳት እንፍጠርለት››
- ዘፍ3÷22 ‹‹እግዚአብሔር አምላክም አለ እነሆ አዳም መልካምና ክፉን ለመወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፡፡››
- ዘፍ11÷6 ‹‹...እግዚአብሔርም አለ እነሆ እነርሱ አንድ ወገን ናቸው፡፡ ለሁሉም አንድ ቋንቋ አላቸው፡፡ ኑ እንውረድ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋውን በዚያ እንደባልቅባቸው››
- ዘፍ18÷1 ‹‹ዓይኑን አነሳና አየ፣ እነሆም ሦስት ሰዎች ወደ እርሱ ቀረቡ ባያቸውም ጊዜ ከድንኳኑ ደጅ ሊቀበላቸው ሮጦ ወደ ምድርም ሰገደ›› - **ሶስትነት**
  ‹‹አቤቱ በፊትህ ሞገስን አግኝቼ እንደሆነ እለምንሀለሁ፡፡ ባሪያህን አትለፈኝ አለ›› **አንድነት**
- ዘጸ3÷6 ‹‹አምላክ፣ አምላክ፣ አምላክ›› **ሶስትነት**
  ‹‹እኔ የአባትህ የአብርሃም አምላክ፣ የይስሐቅ አምላክ፣ የያዕቆብ አምላክ ነኝ አለው፡፡›› (መዝ 32÷5-6)
- ኢሳ6÷3 ‹‹ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ የሰራዊተ ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ ከክብርሩ ተሞልታለች››

በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት

- ማቴ3÷16-17 ‹‹ በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነውና›› ብሎ እግዚአብሔር አብ፣ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል ሲወርድታይቷል ፣ ወልድ በተለይ አካሉ በዮርዳኖስ ባህር ሲጠመቅ ታይቷል፡፡
- ማቴ17÷5 ‹‹የምወደው ልጄ ይኼ ነው እርሱን ስሙት›› ሲል
  - አብ በደመናሆኖ ሲናገር
  - ወልድ በተለይ አካሉ በታቦር ተራራ ቆሞ
  - መንፈስ ቅዱስ በብርሃን አምሳል
- ማቴ28÷19 ‹‹እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁን ሁሉ .... ደቀ ምዛሙርት አድርጓቸው››
  ራዕይ 14÷1 ፣ 1ጴጥ 1÷1፣ 2ቆሮ 13÷14 1ዮሐ 5÷7፣

❖ **የምስጢረ ሥላሴ ምሳሌዎች**

✓ የሰው ተፈጥሮ - ከአራቱ ባህሪያተ ስጋ
- ከሶስቱ ባህሪያተ ነፍስ

ነፍስ በአካሏ የምትከፈል ሶስት ከዊን አላት- ልብነት (አብ)
-ቃልነት(ወልድ)

- እስትንፋስነት(መንፈስ ቅዱስ)

- **የፀሐይ ተፈጥሮ ክበቡ - አብ**
  ብርሃኑ - ወልድ
  ሙቀቱ - መንፈስ ቅዱስ
- **የእሳት ተፈጥሮ አካሉ - አብ**
  ብርሃኑ- ወልድ
  ሙቀቱ-መንፈስ ቅዱስ

ምስጢረ ሥላሴ በሊቃውንት መፃሕፍት

- **ቅዱስ አትናቴዎስ፡-** በሃይማኖተ አበው ክፍል አንድ

‹‹አብ አምላክ ነው፤ ወልድም አምላክ ነው፤ መንፈስቅዱስም አምላክ ነው፤ ነገር ግን ሶስት አማልክት አይባሉም››

- **ቅዱስ ፊላቲዎስ፡-** በሃይማኖተ አበው ክፍል ሁለት

‹‹ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ አብ ልባቸው ነው፤ ለመንፈስ ቅዱስና ለአብም ወልድ ቃላቸው፤ ለአብና ለወልድ ደግሞ መንፈስቅዱስ እስትንፋሳቸው ነው።›› ይገናዘባሉ ማለት ነው።

- **ቅዱስ ኪራኮስ ዘአንጾኪያ ወደማርቆስ ዘእስክንድርያ** በላከው መልዕክት

‹‹አብ ለብቻው የሚሰራ አይደለም፣ ወልድም ለብቻው የሚሰራ አይደለም፤ መንፈስቅዱሰም ለብቻው የሚሰራ አይደለም፤ አብ የወደደውን ወልድና መንፈስ ቅዱስ ይፈጽማሉ ስራቸውም አንድ ነው::››

- **አባ ሕርያቆስ ዘብህንሳ በቅዳሴ ማርያም**

‹‹አብ ወልድና መንፈስ ቅዱስ ያስባሉ፣ ይናገራሉ፣ ይፈቅዳሉ››

ምዕራፍሦስት
ምሥጢረ ሥጋዌ

ትርጓሜ

ሥጋዌ፡ዳሚለው ቃል‹‹**ተሠገው**/ሰው ሆነ/*ሥጋ ነሳ*/››ከሚለው የግዕዝ ግስ የወጣ ሲሆን ትርጉሙም *ሥጋ* መሆን/ሰው መሆን/ማለት ነው።

- በጥቅሉ *ምሥጢረ ሥጋዌ* ስንል ደግሞ ሰውየመሆን/*ሥጋ* የመሆን/ *ምሥጢር* ማለት ነው። በ*ምሥጢረ ሥጋዌ* ትምህርት የምንማረው በ*ምሥጢረ ሥላሴ* ትምህርት ከተመለከትናቸው ከሦስቱ አካላት አንዱ አካል በተለየ ስሙ እግዚአብሔር ወልድ በበደሉ ምክንያት ከክብሩ አንሶ ከፀጋ ተራቁቶ የነበረውን የሰውን ልጅ ለማዳን ከንጽሕት ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከ*ሥጋዋ ሥጋ* ከነፍሳ ነፍስ ነስቶ **<u>ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባህሪይ አንድ ባህሪይ በመሆን ሰው ሲሆን አምላክ፡አምላክ ሲሆን ደግሞ ሰው</u>** የሆነበትን *ምሥጢር* የምንማርበት ነው።
- *ምሥጢር* መባሉም የአለማት ሁሉ ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር ይኸንን ዓለም ከፈጠረበት ጥበቡ በሚበልጥ ጥበቡ ሰው ሆኖ ዓለምን ማዳኑ ሲሆን ይኸም ጥበቡ ጥልቅና የማይመረመር እንደሆነ ሊቃውንት አባቶቻችን ያስረዳሉ። በተጨማሪም ሁሉን ማድረግ የሚችለው አምላክ የፈጠረውን የሰው ልጅ *ሥጋ* ተዋሕዶ የሰው ልጅ ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ አሁንም ድረስ በሰው ልጅ ላይ ደርሶ የማያውቀውን መከራ በመቀበል የድኅነት ስራውን በመፈፀም ነው።

- እግዚአብሔር አምላክ በስድስት ቀናት ውስጥ ከፈጠራቸው ሃያ ሁለት ፍጥረታት መካከል ሁለቱን ማለትም ሰውንና ቅዱሳን መላእክትን አዋቂ፤አስተዋይ ዘለዓለማዊ በማድረግ ስሙን እንዲቀድሱ፡ክብሩን እንዲውርሱ ፈጥሯቸዋል፡፡
- ከእነዚህም ሁለት ፍጥረታት የሰውን ልጅ ከአራቱ ባህርያተ ሥጋና ከሶስቱ ባህርያተ ነፍስ አክብሮና አንፅቶ በአርአያውና በአምሳሉ ፈጥሮታል፡፡ይኸውም ክብሩ እንዲታወቅ አንዳንዱን ሥነፍጥረት በማሰብ ሲፈጥር የተቀሩትን ደግሞ በመናገር /በነቢብ/ ሲፈጥር የሰውን ልጅ ግን ለእርሱ የሚያስፈልጉትን ፍጥረታት ከፈጠረ በኋላ በስተመጨረሻ በእጁ በማበጀት ሕያዊት፤ነባቢት፤ለባዊት ነፍስን እፍ በማለት የፍጥረታት ሁሉ ገዢ፤አስተዳዳሪ አድርጎ ሾሞ ሸልሞ ፈጥሮታል፡፡
- እንዲህ ባለ ክብርና ጸጋ የተፈጠረው የሰው ልጅ ምንም እንኳን የፍጥረታት ገዢ አስተዳዳሪ ሆኖ ቢሾምም እርሱም ፍጥረቱን እንዳይረሳ ለፈጣሪው የሚገባውን ክብር መስጠቱንም እንዳይዘነጋ የምታደርግ በገነት ውስጥ እግዚአብሔር አምላክ ሕግን አስቀመጠ፡ :
- ይህችውም ህግ የአዳምን ፍጡርነት የእግዚአብሔርን ደግሞ ፈጣሪነት የምታሳውቅ ሆና በዕፅ መልክ የተዘጋጀች ሲሆን በገነት ውስጥ ካሉ ብላ ተብሎ ከታዘዘው ዕፅዋት ተለይታ አትብላ የምትለውን የእግዚአብሔርን ሕግ ይዛለችና ሕግን የያዘች ዕፅ ተብላለች፡፡ዘፍ2÷17
- ይሁንና በዚህ ትዕዛዝ ፀንቶ መኖር የቻለው ግን ለሰባት ዓመት ብቻ ነበር፡፡ይኸውም የሰው ልጅ ምክረ ከይሲን ሰምቶ ነፃ ፍቃዱን ተጠቅሞ ህገ እግዚአብሔርን በመተላለፍ ምክንያት ከቀደመው ክብሩ ተዋርዶ የተሠጠውን ጸጋ በማጣቱ በባህሪው ጎሰቆለ ገነትን ያህል ቦታ እግዚአብሔርንም ያህል ጌታ አጣ፡፡ቢሆንም ግን የሰው ልጅ ጥፋቱን አምኖ ንስሐ ገብቶ በሱባኤ ተወስኖ ወደ እግዚአብሔር ምህረትና ይቅርታን በመጠየቁ መሃሪና ይቅርባይ እግዚአብሔር ፍጹም የሆነ ዘለዓለማዊ ምህረትን ከ5 ቀን ተኩል በኋላ ሰው ሆኖ እንደሚሰጠው ቃል ገብቶለት ነበርና ይህንን ቃሉን ለመፈፀም በቀጠረው የቀጠሮ ወቅት ሰው ሆኖ ፍፁም ይቅርታንና ምህረትን ሰጥቶታል፡፡

ስለዚህም እግዚአብሔር ወልድ ሰው የሆነበት ምክንያት

1.ለካሳ፦ካሳ የበደለውን ወገን ለተበዳዩ የሚያቀርበው በጎ ምላሽ ነው፡፡ የበደለው አዳም ነው፡፡ በበደሉም ምክንያትም የሞት ቅጣት ደርሶበታል፡፡ በትክክለኛው ትርጓሜ መሰረት ከተፈረደበት ፍርድ ለመዳን ካሳ መክፈል የሚገባው አዳም ነበር፡፡ታዲያ ከተፈረደበት ሞትለመዳን ለኃጢአቱ ማስተስሪያ ብሎ ለእግዚአብሔር የሚያቀርበው ነገር የለውም፤እርሱ ራሱ የእግዚአብሔር ነውና ስለዚህ የኃጢአት ዋጋው ሞት ከሆነ የሰው ልጅ ሁሉ ራሱ ባመጣው ኃጢአት ከመሞት በቀር ሌላ ምርጫ አልነበረውም ማለት ነው፡፡

እግዚአብሔርም የአዳምን ንስሐና የገባለትን ቃልኪዳን በማሰብ ስለእርሱ ተገብቶ ሊክስለት እግዚአብሔር ወልድ ሰው ሆነ፡፡ምክንያቱም የበደለው ወገን ሰው ነውና፤ፍርዱም የተላለፈው በሰው ላይ በመሆኑ የሚክሰው

- ሰው ሆኖ የሰውን ዘር የሚወክልና ስለ ሰው ልጆችም ተወክሎ ቅጣትን የሚቀበል መሆን አለበት
- የበደለው ሞት ስለተፈረደበትና የተፈረደበትን ሞት በራሱ ሀይልና ጥረት ማራቅ ስለማይችል የሚክሰው መሞት አለበት፡፡

- የሚክሰው ኃጢአት የሌለበትና ንፁህ ባህርይ መሆን አለበት፡፡ነገርግን እርሱም ኃጢአተኛ ከሆነ ስለኃጢአተኞች ካሳ መሆን አይችልም፤እንዲያውም ለራሱ የሚክስለት ያስፈልገዋል፡፡
- የሚክሰው ፈጣሪ መሆን አለበት፤ምክንያቱም የበደለው ሰው የፈጠረው ራሱ ፈጣሪ ነውና ወደ ወህኒ የተጋዙትን ነፍሳት ነፃ ማውጣት የሚችል ፈጣሪ ብቻ ነው፡፡
- የረከሰውን የሰው ተፈጥሮ የሚቀድስና እንደቀድሞ አዲስ ሰውነት የሚሰጠው ፈጣሪ ብቻ ነው፡፡

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን ሁሉ የሚያደርግ ፈጣሪ ብቻ ነውና እግዚአብሔር ወልድ መከራና ሞትን ለሚስማማው ለሰው ባህርይ መከራ ለመቀበልና መስዋዕት ለመሆን ከዚያም መከራ ተቀብሎና መስዋዕት ሆኖ ሰውን ከተፈረደበት ፍርድ ለማዳንና ሊክስለት በመወለድ ግብሩ የሰውን ስጋ ተዋሕዶ ሰው ሆነ፡፡ሮሜ8÷3

2.የዲያቢሎስን ጥበብ በአምላካዊ ጥበብ ሊሸር ነው፡-

እግዚአብሔር የሁሉ ፈጣሪ ነው፡፡በመሆኑም ጠቢበ ጠቢባን(የጠቢባን ሁሉ ጠቢብ)ይባላል፡፡ ዲያቢሎስ በክፋት ተነሳስቶ በጥበቡ አዳምና ሄዋን ትዕዛዝን እንዲያፈርሱ አድርጓል፡፡ጥበቡም በራሱ አካል ቢገልጽላቸውም ጠላት መሆኑን ስለሚያውቁ ለስህተት እንደማይዳረጉ ስለሚያውቅ በእባብ ሥጋ ተሰውሮ አሳታቸው፡፡

እግዚአብሔር በማይመረመር ጥበቡ አዳምን ለማዳን ደካማውን የሰው ስጋ ተዋሕዶ ተገለጠ፡፡ፈጣሪ መሆኑን ሰይጣን እስኪጠራጠር ድረስ ደካማ ሆኖ ቀረበ፡፡ጌታ ተአምራትን ሲያደርግ‹‹**ያለ ጊዜያችን ልታጠፋን መጣህን››በማለት** ሲናገሩ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሲራብ፤ሲጠማ፤ሲያንቀላፋ…ሲያይ ግራ ይጋባ ነበር፡፡ጌታ በመጨረሻ የሰውን ልጅ ፍጹም የሚያድንበት ጊዜ ሲደርስ በዕለተ አርብ ሰይጣንን ለማቅረብና በፍቃዱ የማረካቸውን ነፍሳት እንዲመልስ በመስቀል ላይ ሆኖ‹‹**አምላኬ አምላኬ ስለምን ተውከኝ››በማለት** ሲናገር ፍጡር መስሎት ቀረበ፡፡ጌታችንም ሰውሮበት የነበረውን መለኮታዊ ክብሩን ሲገልፅ ከመስቀል ስር ቅዱሳን መላእክት ሲሰግዱለት ተመለከተ፡፡እርሱንም በነፍሳት አውታር በእሳት ሰንሰለት ወጥሮ ያዘው፡፡ዲያቢሎስም መሸነፉን አመነ፡፡ከእርሱም በበለጠ ጥበብ ክርስቶስ እንዳሸነፈው ተረዳና እንደህ አለ‹‹**ሥጋን ለብሶ ሳየው ፍጡር የመሰለኝ ምዕመናን የነጠቀኝ፤በእጀ ጭብጥ በእግሬ እርግጥ አድርጌ ይዣቸው የነበሩትን ነፍሳትን እንዳልሰለጥናባቸው ያረገኝ ለካስ ሰማያዊ ሆኖል፡፡ ››በማለት** ከእንግዲህ ወዲህ በእርሱ ባመኑ ሰዎች ላይ ምንም አይነት ጥፋት ማድረግ እንደማይችልና ፈፅሞ ድል መሆኑን መስክሯል፡፡ቆላ2÷14 1ኛዩሐ3÷8

3.የሰውን ልጅ ከጠፋበት ለመፈለግ ነው፡-

እግዚአብሔርን በድሎ ከዕፀ በለስ በታች የተደበቀውን አዳምን ጠርቶ‹‹**ወዴት ነህ››**በማለት እግዚአብሔር ፈለገው ዘፍ3÷10 አዳም የተሸሸገበት ቦታ ጠፍቶት ሳይሆን የጠፋው አዳምን ለመፈለግ አላዋቂ ሥጋን እንደሚዋሐድ ሲያጠይቅ ነው፡፡በዘመነ ሥጋዌውም ይህንን ትንቢት ለማጠየቅ አልአዛርን ለማስነሣት እህቶቹን ‹‹ከወዴትአኖራችሁት››ብሏል፡፡የሰውን ልጅ ከጠፋበት ለመፈለግ እንደመጣም ጌታ ራሱ ሲናገር‹‹የሰው ልጅ የጠፋውን ለማዳን መጥቶአልና ምን ይመስላችኋል፤ለአንድ ሰው መቶ በጎች ቢኖሩት ከእነርሱም አንዱ ቢባዝን ዘጠና ዘጠኙን በተራራ ትቶ ሄዶም የባዘነውን አይፈልግምን?እንደዚሁ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ በሰማያት ያለው አባታችሁ ፈቃድ አይደለም፡፡››ብሏል ማቴ18÷12-14

4.የሰውን ልጆች ሊያዩት ይመኙ ስለነበር ነው

ወንጌላዊው ቅዱስ ዩሐንስ ‹‹**መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድስእንኳ የለም፤በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው**፡፡››በማለት እግዚአብሔርን በመለኮታዊ ባህርይ ማንም እንዳላየው ነገርግን የሰው ልጆች ሁሉ ሊያዩት ይመኙ ስለነበር የሰውን ሥጋ ተዋህዶ እንደተገለጸ አስረድቷል፡፡ ዩሐ1÷18 ሙሴ‹‹እባክህ ክብርህን አሳየኝ››በማለት ይለምነው ነበር፤እግዚአብሔርም ‹‹ሰው አይቶኝ አይድንምና ፊቴን ማየት አይቻልህም››ዘጸ33÷20 የሰውን ምኞትና ፍላጎት ለሚሚላት ሀያሉና ገናናው አምላክ ሰው ሆነ፡፡ በዘመነ ሥጋዌው ሲያስተምር ይከተሉት ከነበሩ ከ5 የገበያ ሕዝብ መካከል የተወሰኑት መልኩን ለማየት የሚከተሉት ነበሩ፡፡እጅግ ውብ ነበርና ነው ፊቱን ለሙሴ እንደሚያሳየውም ‹**የእግዚአብሔርን መልክ ያያሉ**›ብሎበተናገረው መሰረት ሊያየው ይመኝ ለነበረውሙሴ በደብረ ታቦር ታይቶታል፡፡ዘኁ12÷8 ማቴ17÷3 የሰው ልጅ ፈጣሪውን አየ፤ከእርሱም ተማረ፤ከእርሱ ጋር አብሮ ተመገበ፤ፊቱንም በአይኖቹ አየ፤በዚህም ምኞቱ ተፈፀመ፡፡1ኛ ዩሐ1÷1-4

5ለሰው ልጅ የሰጠውን ተስፋ ለመፈፀም ነው፡፡

አዳምና ሔዋን በድለው እግዚአብሔር እባብን ሲረግም በእርግማኑ መካከል ለአዳም በረከትና ተስፋ ነበር፡፡ ይህንን በረከትና ተስፋ ለመፈፀም ሰው ሆነ፡፡ ተስፋውም እግዚአብሔር እባብን ‹‹በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘርዋም መካከል ጠላትነትን አድርጋለው እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል፤አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ›› ዘፍ 3፡15-16ብሎታል ይህምማለት በአንተ ሲል ዲያብሎስን፣ሴቲቱ ሲል እመቤታችንን፣በዘርህ ያለው የዲያብሎስ ግብር ተከታዮች በሆኑት፤በዘሯ ሲል ከእመቤታችን ለተወለደው የጌታችንን መንገድ ለሚከተሉት ለማለት ነው፡፡ እርሱ ራስን ይቀጠቅጥሃል ማለቱ ጌታችን ዲያብሎስን ቀጥቅጦ ድል እንደሚያደርገው አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ ማለቱ ዲያብሎስን የጌታችንን ተከታዬች ያሳድዳል ማለቱ ነው፡፡ ልዑል እግዚአብሔር ለአባብ ስጋ ተሰውሮ የነበረውን ዲያብሎስን በምስጢር በሚረግምበት ጊዜ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማሪያም በድንግልና ያለ አባት የሚወለደው ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዲያብሎስን በመስቀል ቀጥቅጦ ድል እንደሚያደርገው ለሰው ልጅ ታላቅ ተስፋ ሰጥቶታል፡፡ ይህንን ተስፋ ለመፈፀም እግዚአብሔር ወልድ ሰውሆነ፡፡ የተስፋው ቀን ሲደርስ ጌታ በመስቀል ተሰቅሎ ዲያብሎስን ድል አድርጎ የሰው ልጅ ይህንን የነበረውን ድህነት አብስሮታል፡፡

እግዚአብሔር ወልድ ለምን በተለየ አካሉ ተወለደ?

1. ወልድ በቀደመ ግብሩ ተወላዲ ነው፡፡
2. በደኃራዊ ልደቱ ቀዳማዊ ልደቱን ለማስረዳት

ወልድ እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ ሁለት ልደታት አሉት፡፡ ቀዳማዊ እና ደኃራዊየምንለው

- **ቀዳማዊ ልደቱ** አለም ከመፈጠሩ ዘመን ከመቆጠሩ በፊት ያለው ነው፡፡

የሰው ህሊና ለማይመረምረው ምስጢር እግዚአብሔር ወልድ በተለየ አካሉ ከባህርይ አባቱ ከአብ ያለእናት የተወለደው ነው፡፡ይህ ልደቱ እንደ ሰው /ፍጡር/ ልደት መቅደም መቀዳደም መብለጥና መበላለጥ የለበትም፡፡ እግዚአብሔር ወልድ ከባሕርይ አባቱ ከእግዚአብሔር አብ ተወለደ ስንል እንዴት ነው ቢሉ አብን አክሎ አብን መስሎ(ባህርይ) ከአብ ተገኘ ማለት ነው፡፡ ይህም ባለማነስ ፣ባለመብለጥ ፣ባለመለያየት ፣ባለመለዋወጥ ነው፡፡‹‹ተራሮች ገና ሳይመሰረቱ ከኮረብቶችም በፊት እኔ ተወለድሁ›› ምሳሌ8÷25 መዝ 109፡3

- **ደኃራዊ ልደቱ** አለም ከተፈጠረ ዘመን ከተቆጠረ /ከ5500 ዓመት / በኋላ ያለው ነው፡፡ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከእናት ያለ አባት የተወለደው ነው፡፡

ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ሰው ሆነ ስንል ከስጋዋ ስጋ ከነፍስ ነስቶ ፍፁም ሰው ሆነ ማለታችን ነው፡፡ ምስጢረሥጋዌ የምንለውም ይህን ከእመቤታችን በደኃራዊ ልደቱ የተወለደውን መወለድ ነው፡፡ ይህ ልደቱ በሚታይ በሚዳሰስ በረቂቅ ሳይሆን በግዘፈት ስጋን በመዋሐድ ነው፡፡

ኢሳ7÷14 ‹‹ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል ፡፡ ድንግል በድንግልና ትጸንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች››፡፡

ይህ ከድንግል የመወለድ ምስጢር ጥልቅና የማይመረመር ቢሆንም ቀዳማዊ ልደቱ የተሰወረ ነበርና በደኃራዊ ልደቱ ተገልጧል፡፡

3. ሥላሴ በአብ ልብነት ይቅር ያሉትን አዳምን በወልድ ቃልነት ለመግለፅ

እግዚአብሔር ወልድ ሰው እንደሚሆን የተነገሩ ትንቢቶችና የተመሰሉ ምሳሌዎች

❖ **ትንቢቶች**

- ዘፍ3÷22 ‹‹እግዚአብሔር አምላክም አለ እነሆ አዳም መልካምና ክፉን ለማወቅ ከኛ እንደ አንዱ ሆነ››እግዚአብሔር ራሱ የተናገረው ትንቢት ነው፡፡ ለኋለኛው ዘመን ከሶስት አካላት አንዱ እግዚአብሔር ወልድ የአዳምን ባሕርይ ባሕርዩ አድርጎ እንዲሚወለድ አስቀድሞ የተናገረው ትንቢት ነው፡፡ ክርስቶስ ዳግማዊ አዳም ተብሏል፡፡ **1ቆሮ15÷42-50** ይህ ከድንግል ማርያም የተወለደው አምላክ የአዳምን አካልና ባሕርይ ገንዘቡ እንዳደረገ ማስረዳቱ ነው፡፡

- ዘ ፡24÷17‹‹አየዋለሁ አሁን ግን አይደለም፣እመለከተዋለሁ በቅርብ ግን አይደለም ከያዕቆብ ኮከብ ይወጣል›› ትንቢቱን የተናገረው በለዓም ነው፡፡ ከረጅም ዘመናት በኋላ የያዕቆብ ትውልድ ከሆነች ከእመቤታችን ኮከብ /ኢየሱስ ክርስቶስ / እንደሚወለድ መናገሩ ነው፡፡ ይህ ትንቢትም እንደተፈፀመ ጌታ ሲናገር ‹‹እኔ የዳዊት ስር እና ዘር ነኝና የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ›› ብሏል ራዕ22÷16

ኢሳ 53÷5-12 ‹‹እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ ስለ በደላችን ደቀቀ የድህነታችንም ተግሳፅ በእርሱ ላይ ነበር፡፡ በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን፡፡ እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ››ሰው ሆነ ራሱን ስለእኛ አሳልፎ መሥጠቱን አስቀድሞ የተናገረው ነው፡፡

ከእነዚህ ትንቢቶች በተጨማሪ ሌሎችም ተናግረዋል፡፡ሐዋ8÷32-36፣1ጴጥ2÷22-25፣ዘፍ 3÷15፣መዝ21÷16-18፣ዩሐ19÷23-24፣መዝ2÷6፣106፡1፣131፡6፣73÷12ኢሳ7÷14፣ኢሳ9÷6

❖ **ምሳሌዎች**

-ዘፍ 22፥13 ‹‹ አብርሃም ዓይኑን አነሣ በኃላውም እነሆ አንድ በግ በዱር ውስጥ ቀንዶቹ በዕፅ ሳቤቅ ተይዞ አየ፣ አብርሃም ሄደ በጉንም ወሰደው በልጅም ፈንታ መሥዋዕት አድርጎ ሰዋው››ይህ ጌታ ሰው ሆኖ ዓለምን በሞቱ እንደሚያድን የተመሰለ ምሳሌ ነው ፡፡ በጉ የጌታችን ፣ሐረጉ የእመቤታችን ይሰሐቅ የአዳም ዘር፣ የሞሪያ ተራራ የቀራንዮ ምሳሌ ነው ፡፡ በጉ በይሰሐቅ ምትክ እንደተሰዋ ኢየሱስ ክርስቶስ በበደሉ ሞት የተፈረደበትን የሰው ልጅ ለማዳን መሞቱን የሚያስረዳ ነው ፡፡ዮሐ 1፥36 ኢሳ53፥7

ዘጉ 21፥8-9 ‹‹እግዚአብሔር ሙሴን እባብን ሠርተህ በዓላማ ላይ ስቀል የተነደፈውም ሁሉ ሲያያት በሕይወት ይኖራል››አለው፡፡ ሙሴም የናሱን እባብ ሰርቶ በዓላማ ላይ ሰቀለ እባብም የነደፈው ሰው ሁሉ የናሱን እባብ ባየጊዜ ዳነ ፡፡ሕዝበ እስራኤል በምድረበዳ ሲጓዙ በእግዚአብሔርላይ አማረው በመናገራቸውእግዚአብሔር እባብን ሰደደ ፡፡ ብዙዎችም በእባብ ተነፈድው ሞቱ ግማሾቹም ታመሙ ፡፡ ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ሲፀልይ የናስ እባብ በዓላማ ላይ እንዲሰቅል አዘዘው እባቡን ያዩት ዳኑ ፡፡

ይህም ምሳሌ ነው እባቡ የተሰቀለበት ዓላማየመስቀል ፣ የናሱ እባብ የጌታችን ምሳሌ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ላመኑት በሃይማኖት ዓይን ላዩት በመሰቀል ተሰቅሎ መድኃኒት ሆኗል ህይወትን ሰጥቷል ። ይህን ምሳሌ ጌታ ተርጉም እንዲህ በማለት ተናግራል ። ‹‹ ሙሴ በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁም በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለምሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዲይጠፋ የሰው ልጅ ይሰቀል ዘንድ ይገባዋል›› ዩሐ 3፥14

በተጨማሪ ስለ ክርስቶስ ሰው መሆን የተመሰሉ ምሳሌዎች መረጃ ጥቅስ 2ኛ ነገ 2፥14-21 ዘጸ3፥1-4፣ 6፣12፥1-51፣17፣ 1ኛቆሮ 10፥4፣ ዩሐ 6፥53፣19:36 ሕዝ 44፥1-3

ምሥጢርተዋሕዶ (የተዋሕዶምሥጢር)

- **ተዋህዶ ፡-** ማለት ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባህርይ አንድ ባህርይ
- **ከሁለት አካል የተባሉት** - ሥጋዊ አካልና ፡ መለኮታዊ አካል ናቸው።
  - ሥጋዊ አካል ፡- የሚዳሰስ፣የሚጨበጥ፣ የሚታይ፣ በቦታ የተወሰን ግዙፍ ነው።
  - መለኮታዊ አካል ፡- የማይታይ፣ የማይደሰስ ፣ በቦታ የማይወሰን ረቃቅ ነው።
    - **አንድ አካል** ስንል የማይታየው ፣ የማይደሰሰው ፣ በቦታ የማይወሰን ፣(ሙልዕ በኩሉ)የሆነው መለኮታዊ አካል ከሚዳሰሰው ፣ በቦታ ከሚወሰነው ስጋዊ አካል ጋር በመዋሃድ አንድ በመሆን ሰው ሆነ እንለላን። (ረቂቁነቱ ግዝፈቱን ግዝፈቱ ረቂቅነቱን ሳያጠፋው በተዐቅቦ በመጠባበቅ ተዋሓዱ አንድ ሆኑ እንላለን።
  - ሁለት ባህርይ የተባሉት ሥጋዊ ባሕርይ እና መለኮታዊ ባሕርይ ናቸው።
    - ሥጋዊ ባህርይ፡-የሚታመም፤የሚደክም፤የሚሞት፤የሚበላ፤የሚጠጣ፤የሚያዝን፤ የሚያለቅስ፤የሚያንቀላፋ ነው።
    - መለኮታዊ ባህርይ፡-የማይታመም፡፤የማይደክም፤የማይሞት፤የማያንቀለፋ ነው።
    - **አንድ ባህርይ** ስንል መለኮት የእርሱ ያልሆነው (የሰጋ) ባህርይ ባህርይ አድርጎ ሰጋም የእርሰ ያልሆነው የመለኮት ባህርይ ባህርይ አድርጎ በተአቅቦ መዋሐድ ነውዮሐ 9፥7-8

የምሥጢረ ሥጋዌ (ምሥጢረ ተዋሕዶ)ምሳሌዎች

1- የሥጋና የነፈስ ተዋሕዶ፡-

2- የጋለ ብረት ፡-አንድ ብረት ፣እሳት ፣ውሰጥ በገባ ጊዜ ብረትነቱን ሳይለቅ በብረቱ ቅርፅ እሳት እንደሚሆን

3-ፍሕም ፡-(የእሳትና የከሰል አንድነት ነው)

- መለኮት ርቀቱን (ምልዓቱን) ሳይለቅ ከውሱኑ ሰጋ ጋር ተዋህዶ የሥጋን ገንዘብ ገንዘብ አደረገ ሥጋም ሥጋነቱን ሳይለቅ በተዋህዶ የመለኮት ገንዘብ ገንዘብ አደረገ

ጌታችን አምላክችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆነ ሰንል

- **እንበለ ውላጤ (ያለመለወጥ)**ውላጤ(መለወጥ)ማለት መለኮትሥጋ ሲለብስመለኮታዊ ባህርይውን ትቶ የሥጋን ባሕርይ ያዘ ። እንደሚሉት አይደለም
  ምሳሌ፡- የሎጥ ሚስት ወደ ጨውነት
  በቃና ዘገሊላ ወደ ወይንነት
- **እንበለ ሚጠት (ያለ መመለስ)**፡-ሚጠት (መመለስ) ማለት መጀመሪያ መለኮት ነበረ ሰው ሲሆን መለኮትነቱን ተወና ሥጋ ብቻ ሆነ።ጨርሶ ደግሞ ሲሄድ ሥጋዊ ባህርይውን ተወና መለኮት ሆነ።እንደሚሉት አይደለም

ምሳሌ፡ዶሙሴ በትር
የግብፅ ውሀ

- **እንበለ ሕድረት(ያለ ማደር)**መለኮቱ *ሥጋ* ውስጥ አደረ እንጂ *ሥጋና* መለኮት ግንኙነት የላቸውም፡፡***ምሳሌ፡-***ዳዊት በማህደር
ሰይፍ በሰገባው፡፡እንደሚሉት አይደለም
- **እንበለ ቱሳኤ (ያለመቀላቀል)** ቱሳኤ መቀላቀል ፣መበረዝ መደባለቅ ፣መከለስ ማለት የአምላካዊነት ባህሪ ከሰውነት ባህሪ *ጋር* ተቀላቀለ ማለት ነው፡፡እንደሚሉት አይደለም
- **እንበለ ,ትድምርት (ያለመደመር ያለመደረብ)** ትድምርት መደረብ ማለትም መለኮት በስጋ ላይ ማደር ማለት ነው፡፡እንደሚሉት አይደለም.
- **እንበለ ቡአዴ (ያለመዋደድ ያለመያያዝ ያለተላጽቆ)** እንደ ብረትና እንጨት እንደሚሉት አይደለም
- **እንበለ ፍልጠት (ከተዋህዶ በኋላ የሚመጣ መለያየት)** ነፍስበና *ሥጋ* ተዋህደዋል ነገር ግን ተፈልጠት ለያቸው፡፡

ምዕራፍ አራት

ምስጢረ ጥምቀት

ትርጓሜ፡-

- **ጥምቀት**፡ የሚለው ቃል «አጠመቀ» ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን ትርጉሙም መነከር፣መዘፈቅ፣ መቀበር፣ ውኃ ውስጥ ገብቶ መውጣት ማለት ነው፡፡
- ጥምቀት ምስጢር መባሉ በሚታይ *ሥርዓት* የማይታይ የእግዚአብሔር ጸጋ ስለሚገኝበት ነው፡፡ ይኸውም ካህኑ በውኃው ላይ ጸሎት ሲያደርግ ይታያል፣ ይሰማል፡፡ ተጠማቂም ውኃ ውስጥ ሲገባና ሲወጣ ይታያል፡፡ ነገር ግን ውኃው ተለውጦ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በተሰቀለ ጊዜ ከጎኑ ወደወጣው ውኃ(ማየ ገቦ) ሲቀየር ግን አይታይም፡፡ ልጁም (ተጠማቂውም) ከእግዚአብሔር ልጅነት ሲያገኝ አይታይምና ምስጢር ተብሏል፡፡

አስፈላጊነት፡-

1. **ዘላለማዊ ድኅነት ያስገኛል፡-**
   ለዚህምማር16÷16 «*ያመነ የተጠመቀ ይድናል*» **በማለት ጌታችን የተናገረውን ማየት በቂ ነው፡፡**
2. ***ዳግም ልደት ይገኝበታል፡-***
   ሰው ከእናትከአባቱ *ለመጀመሪያ* ጊዜ በስጋ ይወለዳል፡፡ ክርስቲያን ደግሞ ዳግም በአርባና በሰማንያ ቀን ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ በጥምቀት የእግዚአብሔር ልጅነትን ያገኛል፡፡
   ለዚህምዮሐ3÷5፡ . . . . «እውነት እውነት እልሀለሁ ዳግመኛ ከውኃና ከመንፈስ ቅዱስ ያልተወለደ ሰው ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም፡፡»እንዲል
3. ***ሥርየተ ኃጢአት ያስገኛል፡-***
   ለዚህም፡- ቅዱስ ጳውሎስ ከአህዛብነት ከእኩይ ምግባሩ ሲመለስ ሐናንያ የመከረውን ምክር እናስተውል

የሐዋ 22÷16 «አሁንስ ስምን ትዘገያለህ? ተነሳና ስሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጢአትህም ታጠብ» ብሎታል። ይኸውም በጥምቀት ፍፁም የሆነ ስርየተ ኃጢአት እንደሚገኝ ሲያመላክት ነው።

በተጨማሪም በቅዱስ ጴጥሮስ ስብከት ልባቸው የተነካ ምዕመናን ምን እናድርግ ብለው በጠየቁ ጊዜ

የሐዋ 2÷38 « ንስሀ ግቡ ኃጢአታችሁ ይሠረይላችሁ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ።» ብሎ ቅዱስ ጴጥሮስ የመለሰውን መልስ ማየት እንችላለን።

4. **አዲስ ሕይወት ይገኛል፡-**

ለዚህም ሮሜ6÷4፡- « እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሳ እንዲሁእኛም በአዲስ ህይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን» በማለት ቅዱስ ጳውሎስ አሮጌው ሰውነት፣ በኃጢአት ያደፈው ማንነት፣ በጥምቀት አዲስ ህይወት እንደሚያገኝ አረጋግጦልናል።

5. **ከክርስቶስ ጋር አንድ እንሆናለን፡-**

ለዚህም ገላ3÷27፡- «ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋል»በማለት ቅዱስ ጳውሎስ በበደል ከተለየነው ከአምላካችን ጋር እንድ የምንሆነው ከክርስቶስ ጋር የምንተባበረው ጥምቀት እንደሆነ ገልጾልናል።

6. **የቤተክርስቲያን አባል እንሆናለን፡-**

ለዚህም ቆላ2÷11-13፡- « . . . በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ . . . እናንተም በበደላችሁና ስጋችሁን ባለመገረዝ ሙታን በሆናችሁ ጊዜ ከእርሱ ጋርሕይወትን ሰጣችሁ...» በማለት በብሉይ ኪዳን የአብርሃም ዘር ለመባል ግዝረት እንደሚያስፈልገው ሁሉ በሐዲስ ኪዳንም የቤተክርስቲያን አባል የመሆናችን ማረጋገጫ ማኅተሙ ጥምቀት እንደሆነ ቅዱስ ጳውሎስ አስረድቶናል።

የጥምቀት ምሳሌዎች በብሉይ ኪዳን፡-

1. **የኖኅ ዘመን ውኃ**

ለዚህም በ1ጴጥ 3÷20-21፡- « ጥቂቶች ማለትም ስምንት ነፍስ በውኃ የዳኑበት መርከብ ሲዘጋጅ በኖኅ ዘመን የእግዚአብሔር ትዕግስት በቆየ ጊዜ ቀድሞ አልታዘዘውም። ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል። . . .» በማለት ቅዱስ ጴጥሮስ የኖኅ ዘመን ውኃ ለሐዲስ ኪዳን ሊመሰረት ላለው ጥምቀት ምሳሌው እንደሆነ አስረድቶናል።

2. **የእስራኤል በኤርትራ ባህር መካከል ማለፍ**

ለዚህም 1ቆሮ 10÷1-2፡- «. . . በባሕር መካከል ተሻገሩ ሁሉንም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ» በማለት እስራኤላውያን ባሕር ኤርትራን አልፈው ምድረርስት እንደገቡ ሁሉ በሐዲስ ኪዳንም ምዕመናን በጥምቀት የእግዚአብሔርን ልጅነት በማግኘት ወደ መንግስተ ሰማያት እንደሚገቡ ገልጾልናል።

3. **ግዝረት፡-**
   ለዚህም፡- ቆላ2÷10-12፡- «የስጋን ሰውነት በመገፈፍ በክርስቶስ መገረዝ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ ደግሞ ተገረዛችሁ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ በጥምቀት ደግሞ ከሙታን ባስነሳው በእግዚአብሔር አሰራር በማመናችሁ ከእርሱ ጋር ተነሳችሁ» በማለት ቅዱስ ጳውሎስ የአብርሃም ዘር ለመባል ግዝረት እንደሚያስፈልግ ሁሉ የክርስቶስ ወገን ለመባልም ጥምቀት እንደሚያስፈልግ በመግለፅ ግዝረት በሐዲስ ኪዳን ለመሰረት ላለው ለጥምቀት ምሳሌ እንደነበር ገልጸልናል፡፡

4. **የንዕማንና፣ የኢዮብ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ከለምጽና ከደዌ መዳን፡-**
   - ኢዮብና ንዕማን የአዳም ምሳሌ፤ ለምጽና ደዌ የመርገመ ስጋ የመርገመ ነፍስ ምሳሌ፤ ዮርዳኖስ ባሕር ደግሞ የጥምቀት ምሳሌ ሲሆን ኢዮብና ንዕማን ከለምጽና ከደዌ በዮርዳኖስ ባሕር ተጠምቀው መዳናቸው ደግሞ አዳምና ልጆቹ በጥምቀት ከመርገመ ስጋ ከመርገመ ነፍስ እንደሚድኑ ሲያስረዳ ነው፡፡ 2ነገ5÷8-14፣

5. **አብርሃም ነገስተ ኮሎዶጎምርን ድል ነሥቶ ሲመለስ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ለማቅረብ ወደ መልከጼዴቅ ሲሄድ ባህረ ዮርዳኖስን መሻገር፡፡**
   - አብርሃም የምዕመናን ምሳሌ፣ መልከጼዴቅ የካህናት ምሳሌ፣ ዮርዳኖስ የጥምቀት ምሳሌ፣ መልከጼዴቅ ለአብርሃም ይዞት የጠበቀው ኅብስተ አኮቴቱ የቅዱስ ስጋው ጽዋ በረከቱ ደግሞ የክቡር ደሙ ምሳሌ ሲሆን አብርሃም ዮርዳኖስን ተሻግሮ ከመልከጼዴቅ ኅብስትና ጽዋዕ መቀበሉ ተጠምቀን የክርስቶስን ስጋና ደም እንደምንቀበል ሲያጠይቅ ነው፡፡ ዘፍ14÷17

የጥምቀት አይነቶች

1. **የውኃ ጥምቀት፡-** ይህ የጥምቀት አይነት ጌታችን ለአይሁድ አለቃና መምህር ለኒቆዲሞስ ያስተማረውን መሰረት በማድረግና የምንፈፅመው ነው፡፡ ይሄ ጥምቀት ለህፃናት ከሆነ በ40 በ80 ቀን ሲፈፀም ለአዋቂዎች ግን በአመኑበት ወቅት ሥርዓተ ቤተክርስቲያን በሚያዘው መሰረት ይፈፀማል፡፡ ዮሐ3÷5

2. **በንስሐ ዕንባ መጠመቅ /አንብአ ንስሐ/፡-** ይህ አይነቱ ጥምቀት ከአሕዛብነትና ከአረማዊነት ተመልሰው በክርስቶስ የባህይ አምላክነት ላመኑና በቤተክርስቲያን ስርዓት መሰረት በንስሐ ውስጥ እያሉ በተለያየ ምክንያት ነፍሳቸው ከስጋቸው ብትለይ በንስሐ ህይወት እያሉ ያለቀሱት የንስሐ እንባ እንደጥምቀት ተቆጥሮላቸው የመንግስቱ ወራሽ የስሙ ቀዳሾች ይሆናሉ፡፡

3. **በደም መጠመቅ (ጥምቀት ደም)፡-** ይህ አይነቱ ጥምቀት በሰማዕትነት የሚያርፉ ክርስቲያኖችን የሚመለከት ሲሆን አንድ ክርስቲያን የክርስቶስን የባህርይ አምላክነት አምኖ ስርዓተ ጥምቀት ሳይፈፅምለት በአላውያን ነገስታት በሰማዕትነት ሲሞት የፈሰሰው ደሙ እንደ ጥምቀት ተቆጥሮለት ከእግዚአብሔር ዘንድ ልጅነትን አግኝቶ የመንግስቱ ወራሽ የስሙ ቀዳሽ ይሆናል፡፡

4. የእሳትና የመንፈስ ጥምቀት

የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት

የጥምቀት መሥራች ባለቤቱ ጌታችን አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ይኸውም በ30 ዘመኑ ጥር 11 ቀን እለቱ ማክሰኞ ከሌሊቱ 10:00 ሰዓት በባህረ ዮርዳኖስ በአገልጋዩ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ የጥምቀትን ሥርዓት መስርቶልናል::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን ተጠመቀ?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው ዮሐንስ ህዝቡን ያጠምቅ እንደነበረና ስርየተ ኃጢአት ለማግኘ ትና ከደዌ ለመዳን ሳይሆን ጌታችን የተጠመቀበት ምክንያት:-

1. **ለትሕትና ነው:-** ይኸውም ጌታችን ራሱን ዝቅ አድርጎ በባሪያው በዮሐንስ እጅ በመጠመቅ በማቴ 11÷29 «ከእኔ ተማሩ» ያለውን ትህትናን በቃል በመናገር ብቻ ሳይሆን በተግባር በመፈጸም አሳይቶናል::
2. **ለአርአያነት ነው:-** ይኸም ጌታችን እርሱ ሳያደርገው እኛን አድርጉ (ፈጽሙት) ያለን ምንም ነገር የለም:: በመሆኑም ተጠምቀን እንድን ዘንድ አርአያ (አብነት) ሊሆነን ተጠምቆ አሳይቶናል::
   ለዚህም ዮሐ 13÷12-17 « . . . እኔ እንዳደረግሁላችሁ እናንተም ልታደረጉ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና. . .»
3. **ትንቢቱን ለመፈጸም ነው::** ነቢያት ነብይነታቸው የሚረጋገጠው ትንቢታቸው ሲፈፀም ነውና ጌታም በነቢያት የተነገረውን ትንቢት ሲፈጽምና ትንቢቱን የተናገረውን ነብይ ነቢይ ሊያሰኝ ውተጠምቋል:: ይኸውም በመዝ 76÷16:- «አቤቱ ውኆች አዩህ፤ ውኆችም አይተውህ ፈሩ:: ጥልቆች ተነዋወጡ፤ውኆችም ጮሁ፤ ደመኖችም ድምጽን ሰጡ::» በማለት ቅዱስ ዳዊት የተናገረው ትንቢት ጌታችን በተጠመቀ ጊዜ ፍጻሜውን አግኝቷል::
4. **ተሰውሮ የነበረውን የአንድትና የሦስትነት ምስጢር ለመግለጥ ነው::**
   በብሉይ ኪዳን ጎልቶ የማይታወቀው የሦስትነት ምስጢር ጌታ በዮርዳኖስ ባህር በተጠመቀ ጊዜ በገሀድ ተገልጦ ታይቷል::
   ለዚህም ማቴ 3÷16-17:- « ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ወጣ፤ እነሆ ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣአየ:: እነሆም ድምጽ ከሰማይ መጥቶ«በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው::» የሚል ድምጽከሰማይ መጣ::» በማለት ጌታችን በተጠመቀ ጊዜ አብ በደመና ሆኖ የምወደው ልጄ እርሱን ስሙ ሲል፣ ወልድም በተለየ አካለ በዮርዳኖስ ባህር ተጠምቆ ሲወጣ፣ መንፈስ ቅዱስም በርግብ አምሳል ከሰማይ ወርዶ በጌታ ራስ ላይ ሲያርፍ በግልጥ የሶስትነት ምስጢር መገለጡን ወንጌላዊው ቅዱስ ማቴዎስ አስረድቷል::
5. **የዕዳ ደብዳቤያችንን ለመደምሰስ ነው:-** አዳምና ሔዋን በምክረ ከይሲ ተታለው በፈቃዳቸው ፈቃደ እግዚአብሔርን በተላለፉ ገነትን ያክል ቦታ እግዚአብሔርን ያክል ጌታ አጥተው በዲያቢሎስ ግዛት ስር ወደቁ:: ዲያቢሎስም መከራውን ካፀናባቸው በኋላ የእርሱ ባርያዎች መሆናቸውን አምነው የባርነት ማረጋገጫ ደብዳቤ **በዕብነ ሩካም**/በዕብነ በረድ/ ላይ ጽፈውቢሰጡት መከራውን እንደሚያቀልላቸው ነገራቸው:: እነርሱም እውነት መስሏቸው በሁለት ዕብነ ሩካም ላይ «አዳም ገብሩ ለዲያብሎስ/ አዳም የዲያብሎስ ባርያ/ ወንድ አገልጋይ/ ፣ ሔዋን ዓመቱ ለዲያብሎስ/ ሔዋን የዲያብሎስ ገረድ/ ሴት አገልጋይ/» ብለው ጽፈው

ሰጥተውታል። እርሱም በራሱ ጥበብ አንዱን አርቆ በዮርዳኖስ ባህር አንዱን ደግሞ አርቆ በሲኦል ውስጥ ሰውሮታል። ስለዚህም ይሄንን የእዳ ደብዳቤ ጌታ በዮርዳኖስ ባህር በተጠመቀ ጊዜ እንደሰውነቱ ረግጦ እንደ አምላክነቱ አቅልጦ አጥፍቶልናል። በሲኦል ውስጥ የሰወረውንም በዕለተ አርብ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ነፍሳትን ሲያወጣ አጥፍቶልናል። ቆላ2÷13-15

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በ30 ዘመኑ ተጠመቀ?

ጌታ ዝቅ ብሎ በ25 ከፍ ብሎ ደግሞ በ32 ዓመቱ ያልተጠመቀው በ30 ዘመን መጠመቅ ያስፈለገበት ምክንያት

1. **የኦሪት ሕግ ለማጽናት ነው**፡- ይሄውም በኦሪት ህግ መሰረት ለክህነት አገልግሎት መመረጥ የሚቻለው በ30 ዘመን እንደነበር ሁሉ እርሱም የሊቀ ካህንነቱን ተግባር፣ የመምህርነቱን ስራ፣ በ30 ዘመን በመጠመቅ በመጀመር ሥርዓተ ኦሪትን አጽንቷል። ዘኁ4÷1-3፣ ዘኁ4÷23፣በዚህም አብነት ይሆን ዘንድ በሐዲስ ኪዳን የክህነት ሹመት በ30 ዘመን እንዲሰጥ ሆኗል።
2. **አዳም የ30 ዘመን ጎልማሳ ሆኖ ተፈጥሮ ያጣውን ልጅነት ለመመለስ በ30 ዘመኑ ተጠመቀ**።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በዮርዳኖስ ባህር ተጠመቀ?

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስበዮርዳኖስ መጠመቁ የአጋጣሚ ጉዳይ ሆኖ ወይም ደግሞ በኢየሩሳሌም አካባቢ ካሉ አፍላጋት የዮርዳኖስ በጥልቀት ስለሚሻል አይደለም። ጌታ በዮርዳኖስ ባህር የተጠመቀበት ምክንያት

1. **ትንቢቱን ለመፈጸም ነው**፡- ጌታ በባህረ ዮርዳኖስ እንደሚጠመቅ አስቀድሞ መዝሙረኛው ቅዱስ ዳዊት በመዝ113÷3-7፡- «ባህር አየች ሸሸችም ዮርዳኖስም ወደኋላ ተመለሰች። ተራሮች እንደ ኮርማዎች ኮረብቶችም እንደጠቦቶች ዘለሉ፤ አንቺ ባህር የሸሸሽ አንቺም ዮርዳኖስ ወደ ኋላሽ የተመለሽ ምን ሆናችኋል? እናንተም ተራሮች እንደ ኮርማዎች ኮረብቶችም እንደ ጠቦቶች ለምን ዘለላችሁ? ከያዕቆብ አምላክ ፊት።።» ለማለት ጌታ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ የሚፈፅማትን ድርጊት በትንቢት መነፅር ተመልክቶ ተናግሮታል።
2. **ምሳሌውን አማናዊ ለማድረግ፡- ይኸውም**
   - የዮርዳኖስ ወንዝ ነቁ (ምንጭ) አንድ ነው። ዝቅ ብሎ ዮርዳኖስ በተባለ በእስራኤልና በአህዛብ መካከል ወደሚገኙ ቦታዎች ይከፈላል፤ ወረድ ብሎ የተለያዩት ይገኛሉ። ይሄ የሚገናኙበት ቦታም ዮርዳኖስ ይባላል። ጌታም የተጠመቀው በዚህ ቦታ ነው።
   - የዮርዳኖስ ወንዝ ምንጩ አንድ መሆነ የሰው ዘር ሁሉ ምንጩ፣ ግንዱ አንድ አዳም መሆኑን ሲያሳይ
   - ዝቅ ብሎ መከፋፈሉም እስራኤል በሕገ ኦሪት አህዛብ ደግ በአምልኮተ ጣኦት ወይም ደግሞ እስራኤል በግዝረት አህዛብ ደግሞ በቁልፋት የመለያየታቸው ምሳሌ
   - ዝቅ ብለ መገኘቱ ደግ ጌታ በጥምቀቱ ህዝብና አህዛብን አንድ የማድረጉ ምሳሌ ነው።
   - ከዚህ በተጨማሪ ከላይ የጥምቀት ምሳሌዎች በብሉይ ኪዳን የሚለውን ማየት ይቻላል።
3. **የዕዳ ደብዳቤያችንን ለመደምሰስ ነው**፡- ከላይ እንደተመለከትነው ዲያብሎስ አዳምና ሔዋን የእርሱ ባርያዎች እንደሆኑ ካመኑለት በኋላ ስመ ግብርናቸውን በሁለት ዕብነ ሩክም/ዕብነ በረድ/ ጽፎ አንዱን በዮርዳኖስ እንደሰወረው ተመልክተናል። ታዲያ በዮርዳኖስ የሰወረው የእዳ ደብዳቤ የሚጠፋው (የሚሰረዘ) ጌታ ግድ በባህሪ ዮርዳኖስ ተጠምቆ ስለነበር ጌታችን

ይህንን የሰይጣን ጥበብ በጥበቡ ሽሮ በባህረ ዮርዳኖስ ሲጠመቅ እንደሰውነቱ ረግጦ እንደ አምላክነቱ አቅልጦ አጥፍቶለታል፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን በውኃ ተጠመቀ?

ጌታችን ጌትነቱን ለመግለጥ ጥምቀቱን በማር ወይም በወተት ወይም በሌላ በከበሩ ፈሳሾች ያላደረገበት የእኛንም ጥምቀት ጨምሮ እርሱም በውኃ የተጠመቀበት ምክንያት ምንድን ነው ቢሉ

1. **ትንቢቱን ለመፈጸም፡-** ይኸውም በነበዩ በቅዱስ ዳዊት አንደበት«ባህር አየች ሸሸችም» በማለት ጌታ በዮርዳኖስ ባህር ሊጠመቅ ሲል የዮርዳኖስ ውኃ የአምላክን ክብረ በዚህ አይነት መልኩ እንደገለፀች ቅዱስ ዳዊት ያስረዳል፡፡ ታዲያ ባህር አንድ የውሀ ክፍል ነውና በነቢያት አንደበት ጌታ በውኃ ተጠምቋል፡፡
2. **ውኃ ለምህረት እንደተፈጠረ ለማጠየቅ፡-**ይህ በኖህ ዘመን የነበሩ ሰዎች/ሰብዓ ትከትን/ ኃለም የግብፅ ሰዎችን /ሰብዓ ግብፅ/ ካጠፋ በኋላ ሰዎች ውሃን ለጥፋት እንጅ ለምህረት እንደተፈጠረ አያስቡም ነበርና ጌታ በውኃ በመጠመቅ እናንተም በውኃ ብትጠመቁ ፍፁም ምህረትን ታገኛላችሁ በማለት ውኃ ለምህረት እንደተፈጠረ አስተምሮናል፡፡
3. **ጥምቀት ለሰው ዘር ሁሉ እንደተሰጠ ለማጠየቅ**፡ ይኸውም ውሃ በሁሉ ቦታ ይገኛል፡ ማርና ወተት ግን በሁሉ ቤትና ቦታ ለማግኘት ሀብትና አቅም ይጠይቃል፡፤ ጌታም ይሄን አውቆ ጥምቀት ደሀን ከሀብታም ሳትለይ ለሁሉ እንደተሰጠች ለማስተማር እርሱ በውኃ ተጠምቆ እኛም በውኃ እንድንጠመቅ ሰርዓት ሰርቶልናል፡፡
4. **በጥምቀት ልምላሜ ስጋ ልምላሜ ነፍስ እንደሚገኝ ሊያጠይቅ፡-** ይኸውም ማርና ወተትን ተክል ላይ ቢያፈሳቸው ተክል ያደርቃሉ ውኃ ግን ተክል ላይ ቢያፈለሱት ተክል ያመልማል እናንተም በውኃ ተጠምቃችሁ ልምላሜ ስጋ ልምላሜ ነፍስን ታገኛላችሁ ሲል እርሱ በውኃ ተጠምቆ እኛ በውኃ እንድንጠመቅ ስርዓት ሰርቶልና፡፡
5. **ጥምቀት ከኃጢአት እድፍ እንደምታጠራ ለማጠየቅ**፡- ይኸውም ማርና ወተት ልብስ ቢያጥቡባቸው እድፍ አያጠሩም ውኃ ግን ልብስ ቢያጥቡበት ያጠራል፡፤ እናንተም በውኃ ብትጠመቁ ከኃጢአት እድፍ ትጠራላችሁ ሲል በውኃ ተጠምቋል፡፡
6. **በጥምቀት ከገኃነም እሳት ትድናላችሁ ሲል ነው**፡ ይኸውም ውኃ እሳት ያጠፋል እናንተም በባህሪይ አምላክነቱ አምናችሁ በውኃ ብትጠመቁ ከገሀነመ እሳት ትድናላችሁ ሲል በውኃ ተጠምቋል፡፡
7. **በጥምቀት መልክአ ሥላሴን ታያላችሁ ሲል ነው፡፡**ይኸውም ውኃ ከሌሎች ፈሳሶች ይልቅ መልክን ያሳያል፡፡ እናንተም በውኃ ብትጠመቁ መልክአ ሥላሴን /የሥላሴ መልክን/ ታያላችሁ ሲለን በውኃ ተጠምቋል

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በቅዱስ ዮሐንስ እጅ መጠመቁ ስለምንድነው? ቅዱስ ዮሐንስና ጌታ ዝምድና ሲኖራቸው በ6 ወራትም ቅዱስ ዮሐንስ ጌታችንንበውልደት ይበልጠዋል፡፡ ቅዱስ ዮሐንስ በወቅቱ ህዝቡን ያጠምቅ የነበረው ጥምቀት ኋላ በክርስቶስ ጥምቀት አማካኝነት የሚሰጠውን መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል በቅተው እንዲገኙ የሚያደርግ የንስሐ ጥምቀት ነበር፡፡ ታዲያ ጌታችን በዮሐንስ እጅ መጠመቁ ስለምንድን ነው ቢሉ?

ጌታ ሊጠመቅ ወደ ባህረ ዮርዳኖስ ገብቶ በዮሐንስ ፊት ሲቆም ዮሐንስ እኔ በአንተ ልጠመቅ ይገባናል እንጂ አንተ በእኔ ልትጠመቅ ይገባሃልን በማለት ይከራከረው ነበር::ጌታም ለዮሐንስ እንዲህ ሲል መልሶለታል:: «አሁንስ ፍቀድልኝ እንግዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልናአለው» ማቴ3÷15-16 ጌታ ይሄን ማለቱ እኔ በፈጠረው ፍጥረት እጅ ተጠመቀ ተብዬ ትህትናዬ ይነገርልኛል አንተም መጥምቀ መለኮት/አምላክን ያጠመቀ/ ተብለህ ንፅህናህ ቅድስናህ እስከ አለም ፍፃሜ ሲነገር ይኖራል ሲለው ነው:: በዚህ ጊዜ ዮሐንስ ሰዎችን በአንተስም፣ በባህሪ አባትህና በባህሪ ህይወትህ በመንፈስ ቅዱስም አጠምቃቸዋልሁ:: አንተን በማንስም ላጥምቅህ ብሎ በጠየቀው ጊዜ «ወልዱ ለቡሩክ ከሳቴ ብርሃን ተሰሃለነ አንተ ከህኑ ለአለም በከመ ሲመቱ ለመልከጼዴቅ/ ብርታንን የምትገልፅ የቡርክ የአብ የባህርይ ልጅ ሆይ ይቅር በለን እንደ መልከጼዴቅ ስርዓት አንተ ለዘላለም ካህንነህ/» እያልክ አጥምቀኝ ብሎ ቅዱስ ዮሐንስ በዚህ መሰረት አጥምቆታል::

ቅዱስ ዮሐንስ ጌታን ሲያጠምቀው እጅን ራሱ ላይ ሳያስነካ ያጠመቀው ስለምንድነው?

1. መስዋዕተ አሪት አለፈ አዲሱ መስዋዕታችን አንተነህ ሲል ነው:፤
2. እጁን ጭኖበት ቢያጠምቀው ኖሮ ኋላ የሚነሱ መናፍቃን እጁን ሲጭንበት ከበረ ባሉ ነበር ነገር ግን ይህ ችግር እንዳይፈጠር አርቆ ሲያጥረው ቅዱስ ዮሐንስ እጁን እንዳይጭንበት አድርጎታል
3. አካለ መለኮትን መንካት አይቻልም ሲል ነው::

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ መቅደስ ዮሐንስ ዘንድ ሄዶ መጠመቁ ስለምንድን ነው?፤- ጌታ ወደ ዮሐንስ ዘንድ ሄዶ የተጠመቀበት ምክንያት

1. **ለትህትና ነው**:: ይኸውም እርሱ መምህረ ትህትና ነውና ከእኔተማሩ ያለው አንዱ ትህትና ስለሆነ ለእኛ ትሁታን ሁኑ ሲል ወደ ዮሐንስ ዘንድ በመሄድ ተጠምቋል::
2. **ሥርዓትን ሲመሰርት ነው**:: ይኸውም ጥምቀት በቅድስት ቤተክርስተያን መፈፀም እንደሚገበው ሲሆን ኃላ የማነሱ ነገስታቱ፣ ሹማምንቱ መኳንንቱና ትላልቅ ሰዎች ኑና አጥምቁን ብለው ካህናትን እንዳያሰቸግራቸው ሥርዓትን ሲሰራ ወደ ዮሐንስ ዘንድ ሄዶ ተጠምቋል::

የክርስትያኖች ጥምቀት

የክርስቶስን የባህርይ አምላክነት የሚያምኑ ክርስቲያኖች ህፃናት ከሆኑ በ40ና በ80 ቀናቸው አዋቂዎች ከሆኑ ደግሞ በአመኑበት ወቅት ሥርዓተ ቤተክርስቲያን በሚያዘው መሰረት ተጠምቀው የእግዚአብሔርን ልጅነት ያገኛሉ::

ይህቺ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ዘንድ ልጅነትን የሚያገኙባት ጥምቀት አንዲት ስትሆን ሥርዓተ ጥምቀቱን መፈፀም የሚገባቸውም ከቅስና በላይ ስልጣነ ክህነት ያላቸው አባቶች መሆን እንዳለባቸው ሥርዓተ ቤተክርስቲያን ያዛል::

ሕፃናት ነፍስ ሳያወቁ በ40ና በ80 ቀናቸው የሚጠመቁት ስለምንድነው?

ጌታ በማር16÷16:- «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ብሎ የተናገረውን ጥቅስ በመያዝ የህፃናትን ጥምቀት ነፍስ ሳያውቁ በአርባና በሰማኒያ ቀን መፈፀሙን የሚቃወሙ አካላት አሉ:: ቅድስት ቤተክርስቲያን ህፃናትን በ40 እና በ80ቀን ስታጠምቅ ህፃናቱ ነፍስ አለማወቀቸው ሳትረዳ ቀርታ ሳይሆን:-

1. ከላይ በማርቆስ ወንጌል ላይ «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» ብሎ ጌታ የተናገረው ለእነማን እንደሆነ ስለምታውቅ ነው፡፤ ይህን ጥቅስ ጌታችን የተናገረው በተለያየ ምክንያት ማለትም ከአህዛብ ወይ ደግሞ የተለያየ ሥርዓተ አምልኮ ካላቸው ቤተሰብ ተወልደው በህፃንነታቸው ስርዓተ ጥምቀት ላልተፈፀመላቸው ሰዎች ሲሆን እነዚህ ሰዎች ስርዓተ ቤተክርስቲያን በሚያዘው መሰረት ቢያንስ ለሁለት አመታት የሃይማኖት ትምህርትንና፣ ስርዓተ ቤተክርስቲያንን ሲማሩ ከቆዩ በኋላ በልቡናቸው ያ የቀድሞ መጥፎ ስሜትና ባዕድ አምልኮ ሲጠፋላቸው (ሲያምኑ) ስርዓተ ጥምቀት ይፈፀምላቸዋል፡፤ ማመን ቀድሞ የሚመጣው እንደነዚህ ላሉ ሰዎች ነው።
2. **የወላጆቸው እምነት ለልጆቹ ይቆጠራል ብላ ስለምታምን ነው።**
   ለዚህም በብሉይ ኪዳን በአብርሃም ቃልኪዳን ያመኑ ሰዎች ልጆቻቸውን የጥምቀት ምሳሌ የሆነችውን ግዝረት የሚፈፅሙላቸው በ8 ቀናቸው ነበር፡፤ ይሁንና ልጆቹ የአብርሃም ዘር መሆናችውንና ለአብርሃም የተሰጠውን ቃልኪዳን አውቀውና አምነው ሳይሆን ስርዓተ ግዝረቱ የሚፈፀምላቸው የወላጆቻቸው እምነት ለልጆቹ ተቆጥሮ ነው። ልክ እንደዚሁም ሁሉ ወላጆች የክርስቶስ የባህርይ አምላክነትን አምነው በመጠመቅ የእግዚአብሔር ልጅነትን ያገኙ ከሆነ የወላጆቻቸው እምነት ለልጆቹ ተቆጥሮ በ40ና በ80ቀናቸውታጠምቃለች፡፤ ዘፍ17÷12፣21÷4 በተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ቦታዎችም ላይ ቅዱሳን ሐዋርያት ሲያጠምቁ ከነቤተሰቡ አጠመቃቸው ይላል እንጂ «ከሕፃናት በቀር» አጠመቋቸው ያላለው ለዚህ ነው።
   - ቅድስት ቤተክርስቲያንም ህፃናትን ወንዶች ከሆነ ዝቅብላ በ30 ከፍ ብላ በ50 የማታጠምቀው በ40ቀን የምታጠምቀው፣ ሴቶች ከሆኑ ዝቅብላ በ70 ከፍብላ ደግሞ በ90 የማታጠምቀው በ80ቀን የምታጠምቀው ስለምንድን ነው ቢሉ፡-

1. **የአዳምና የሔዋን የልደት ምሳሌ ስለሆነ ነው፡፤**ይኸውም አዳም በተፈጠረ በ40ቀኑ ሔዋን በተፈጠረች በ80 ቀኗ በመላዕክት ምስጋና ታጅበው ወደገነት መግባታቸውን አብነት አድርጋ ህፃናትም በተወለዱ በ40ና በ80ቀናቸው ወደቅድስት ቤተክርስቲያን አባልነት ወደ እግዚአብሔር ልጅነት እንዲቀላቀሉ ስርዓት ሰርታለች ኩፋሌ4÷9
2. **ሕገ ኦሪትን ለማጽናት ነው።** ይኸውም በኦሪት ሕግ መሰረት ወላጆች ሕፃናት ልጆችን በወለዱ ለወንዶች ከሆነ በ40 ቀናቸው ለሴቶች ከሆነ በ80ቀናቸው ከሚሰዋ መስዋዕት ጋር በማድረግ ወደ ቤተመቅደስ ይዘው ሄደው የሚገባው ስርዓት እንዲፈፀም ያደርጉ ነበር ዘሌ12÷1-8 ይህንን አብነት በማድረግ ቤተክርስቲያናችን ምዕመናንን ወላጆች ወንድ ልጅ ከወለዱ በ40 ቀኑ ሴት ልጅ ከወለዱ በ80 ቀኗ ወደ ቤተመቅደስ በመውሰድ የእግዚአብሔርን ልጅነት እንዲያገኙ ስርዓት ሰርታለች።

የክርስቲያኖች ጥምቀት የሚፈፀመው በማን ስም ነው?

ጌታችን ከትንሣኤው በኋላ ለቅዱሳን ደቀመዛሙርቱ ተገልጾ እንዲህ አላቸውበማቴ28÷19፡- «እንግዲህ አህዛብን ሁሉ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም እንድትጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርቴ አድርጓቸው።» በማለት ጥምቀት በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም መፈፀም እንዳለበት አስተምሯቸዋል።

ምዕራፍ አምስት
ምስጢረ ቁርባን

- ቁርባን የሚለው ቃል የሱርስት ሲሆን ትርጉሙ በቁሙ መንፈሳዊ አምኃ፣ መስዋዕት መባዕ፣ ለአምላክ የሚቀርብ ገንዘብ ማለት ነው። (ነገረ ሃይማኖት)
- ምስጢረ ቁርባን ከአምስቱ አዕማደ ምስጢር አንዱ ነው። በእግዚአብሔር አንድነትና ሦስትነት (ምስጢረ ሥላሴ) አምነው በክርስቶስ ደም የተዋጁና በአብ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቁ ምእመናን የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ስጋና ክቡር ደም በመቀበል ምስጢረ ቁርባንን ይፈጽማሉ። ጌታ በቃሉ ፣ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው። ብሎ እንደተናገረ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙን የሚቀበሉ ምዕመናን የዘለዓለም ሕይወት አላቸው። ዮሐ 6÷54 ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በመጀመሪያው የቆሮንቶስ ሰዎች መልዕክቱ ‹‹ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት›› ብሎ እንደገለጸው የምስጢረ ቁርባን ተካፋይ የሆነ ሁሉ ስለ ቅዱስ ቁርባን ትርጉም፣ አስፈላጊነት አፈጻጸም ወዘተ ማወቅ ይጠበቅበታል 1ቆሮ 11÷26 (አዕማደ ምስጢር 1 እና 2)
- በሌላም በኩል ቁርባን ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርብ፤ የሚቀበሉት የሚያቀብሉት ማለት ነው። ስለ እውነተኛ መሥዋዕት የሰው ልጆች የዘለዓለም ህይወት ይወርሱበት ዘንድ ስለተሰጠው ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ምስጢር የምንመለከትበት ክፍል ነው። (ዓምደ ሃይማኖት)

የቁርባን ትርጉምና አስፈላጊነት

ቁርባን ወይም መሥዋዕት ለፈጣሪ ስለኃጢአት ይቅርታ የሚቀርብ መባዕ ወይም ሥጦታ ነው። ለእግዚአብሔር ቁርባንን ወይም መሥዋዕትን ለመጀመሪያ ጊዜ ያቀረበው አዳም ነው። ከዚያም በወቅቱ የነበረውን የመሥዋዕት አቀራረብ ልጆቹ አቤልና ቃየን ተምረው ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቅርበዋል። እግዚአብሔርም የአቤልን መሥዋዕት ተቀብሏል። ዘፍ4÷2-4 በብሉይ ኪዳን ቁርባንም መሥዋዕትም የሚሉ ስያሜዎች በተደጋጋሚ የተገለጹ ቢሆንም ቁርባን የሚል ስያሜ የተሰጠው ከእህል ዘር ለሚቀርበው ሲሆን መሥዋዕት ደግሞ ከእንስሳት ለሚዘጋጀው ነው። ዘሌ9÷1 በብሉይ ኪዳን የሚቀርበው መሥዋዕት እንደ ዓላማው አይነት የተለያየ መጠሪያ አለው።

- የሚቃጠል መሥዋዕት የምንለው ሰውተውት ሳይበሉት ከከተማ ውጭ የሚያቃጥሉት ነው ዘሌ 6÷8 ይህም የሚፈፀመው በአመት አንድ ጊዜ ብቻ ነው።
- የእህል ቁርባንየሚሉት ከእህል ከወይን ተዘጋጅቶ የሚቀርበውን ነው ይህ በየሳምንቱና በየወሩ የሚቀርብ መሥዋዕት ነው። ዘሌ2÷1 ፣ 6÷14
- የድኅነት ቁርባን የሚሉት ሰውተው ወደ እግዚአብሔር አመልክተው ከአሳር ከቸነፈር የሚድኑበት ነበር ቁርባኑ የሚሰዋው መከራ በደረሰባቸው ጊዜ ብቻ ነበር። ዘሌ3 7÷1
- የኃጢአት መሥዋዕት ኃጢአት ለማስተሰረይ የሚሰውት መሥዋዕት ነው። ይኸውም አፍአዊ ኃጢአት ማስተሰረያ ነው ዘሌ4÷1፣ 7÷7
- የበደለ መሥዋዕት የሚሉት ሕዝቡ የበደላቸውን ወይም ጥፋታቸውን ለካህናት ተናግረው ቀኖና የሚቀበሉ ነው።ዘሌ 5፣ 7

እነዚህ የመሥዋዕት ዓይነቶች ከርግብና ከዋኖስ ጀምሮ እስከ ወይፈኖችና ጊደሮች ድረስ ለኃጢአት ማስተሰረያ ይታረዱ፣ ይቃጠሉ፣ ይበሉ የነበሩ ናቸው። በአፈፃፀማቸውም ለሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት ምሳሌና ጥላ ሆነው አልፈዋል ዘሌ 6÷14

ሰው ከበደለ በኋላ ከኃጢአቱ ነጻ የሚሆነው ንስሐ በመግባቱ ብቻ አይደለም። ከንስሐው በኋላ መሥዋዕት ሲያቀርብ ፣ ደም ሊያፈስ የግድ ነው። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ ‹‹**ደም ሳይፈስ ሥርየት የለም**››. ብሎ እንደተናገረው የኃጢአተኛውን በደል የሚሸከም

ወይም ፍርዱን የሚቀበል ሌላ ያልበደለ ነፃ አካል ለመሥዋዕትነት ሊቀርብ ያስፈልጋል፡፡ በብሉይ ኪዳን ብዙ ጥጆችና ጊደሮች፣ በጎችና ፍየሎች ለመሥዋዕትነት ቀርበዋል ሆኖም የሰውን ልጅ ኃጢአት በሙሉ ሊያነጹ አልቻሉም በመሆኑም ራሱ ባለቤቱ ልዑል እግዚአብሔር አንድ ልጁን በመላክ ለመሥዋዕትነት አቀረበው ቅዱስ ኤጲፋንዮስ በቅዳሴው ላይ **‹‹ከአቤል ደም ጀምሮ እስከ በራክዮ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ የፈሰሰው የቅዱሳን ነቢያት ደም ዓለምን ለማዳን እነዳልበቃ ባየ ጊዜ እግዚአብሔር መድኃኒትና ቤዛ የሆነውን አንድ ልጁን ላከልን››** ብሎ እንደገለጸው ጌታችን መድኃኒችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት ሆኖ በመቅረብ በእህልም ሆነ በእንስሳት ይቀርብ የነበረውን የብሉይ ኪዳን መሥዋዕትነት አስወግዶ በራሱ ደም ፍጹም አድርጎታል አንድ ልጁን ላከልን ማለት የሥላሴ ፈቃድ መናገር ነው፡፡ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም እደተናገረው ‹‹እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መስዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ›› ዕብ 10÷12 ይህም መስዋዕት አንድ ጊዜ ከተፈጸመ በኋላ እስከ አለም ፍጻሜ የሚነሱትን ምእመናን ማዳን ትችል ዘንድ በምስጢረ ቁርባን አማካይነት ለቤተክርስቲያን ተሰጠ፡፡

በብሉይ ኪዳን የቁርባን ምሳሌ

መልከ ጼዴቅ በዘመነ አሪት ከቀደምት አበው ሁሉ ለየት ባለ መልኩ በቀራንዮ ኮረብታ ላይ ከእርሱ በፊትም ሆነ ከእርሱ በኋላ እንደሚያቀርቡት የደም መሥዋዕት ሳይሆን በኅብስትና በወይን ያስታኩት (ያመሰግን)ነበርዘፍ 14÷18-20

አብርሃም አምስቱ ነገሥተ ኮሌዶጎሞርን ወግቶ ሲመለስ መልከጼዴቅ ኅብስትና ወይን ይዞ ተቀብሎታል፡፡ በዚህ መሠረት የመልከ ጼዴቅ ኅብስት አኩቴት ጽዋዐ በረከት የሥጋ ወደሙ ምሳሌ ሲሆን መልከጼዴቅ የጌታ አብርሃም የምዕመናን ምሳሌ ነው፡፡ **ዕብ 5÷6**

- እስራኤላውያን ከግብጽ ከመውጣታቸው በፊት ከሞተ በኩር ይድኑ ዘንድ የተመገቡት በግ የቁርባን ምሳሌ ነበር፡፡ እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት ለእስራኤል ልጆች ትእዛዝ ሰጣቸው ‹‹ነውር የሌለበት የአንድ ዓመት ጠቦት እንዲያዘጋጁ እስከ አስራ አራተኛው ቀንም እንዲጠብቁት›› ሲመሽም እንዲያርዱት፣ ከደሙም ወስደው በሚበሉበት ቤት ሁለቱን መቃን እንዲቀቡት በእሳት የተጠበሰውን ሥጋውንና ቋንጣወን እንጀራ በዚያች ሌሊት እንዲበሉ፣ የቀረበውን እሳት እንዲያቃጥሉት . . .››ዘጸ 12-6 በታዘዙት መሠረት ሁሉን አድርገው ከሞት በኩር ድነዋል፡፡ ይህም ሊመጣ ላለው ምሳሌ ነበር
- ነውር የሌለበት የአንድ ዓመት ጠቦትኃጢአት የሌለበት የንጹህ ባህርይ አምላክ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ ነው፡፡ **በጉን በወሩ በአስራ አራተኛው ቀን እንዲሰውት እንዲታዘዙ ሁሉ የጌታም ምክረምቱ በመጋቢት አስር ተጀምሮ በአስራ አራተኛው ቀን ተፈጽሟል፡፡** የበጉ ደም በተቀባበት ቤት ሞተ በኩር እንዳልደረሰ እንዲሁም ዛሬም በመስቀል ላይ ደሙን ባፈሰሰው አምላክ አምኖ ሥጋውንና ደሙን የተቀበለ ሰው የዘላለም ሞት አያገኘውም፡፡ በቤቱ ውስጥ የነበሩት ሁሉ የተጠበሰውን የበጉን ሥጋ እንዲበሉ ታዘው ነበር ጥሬውናነ ቅቅሉን ግን እንዳይመገቡም እንዲሁ፡፡ በእሳት የተመሰለ መለኮ የተዋሐደውን ሥጋ ለምንቀበል ለኛ አብነት ለመሆን የምንበላውና የምንጠጣው ስጋና ደም ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው ነው፡፡

አታሳድሩ ከአንዱ ወደ አንዱ አትውሰዱ መባሉ ምሳሌነቱ የጌታ ስጋው በመስቀል ላይ አለማደሩ ዕለቱን ወደ መቃብር መውረዱን የሚያሳይ ሲሆን እንዲሁም የተቀበረው በተሰቀለበት አቅራቢያ መሆን ያስገነዝባል፡፡ እንደ ቤተክርስቲያናችን ሥርዓት መሥዋዕትን ከአንዱ ሠርቶ ወደ አንዱ ወስዶ መሠዋት የተከለከለው ይህን መሠረት አድርጎ ነው፡፡ የበላችሁትን በልታችሁ የተረፋችን ከእሳት ጨምሩት በተባሉት መሠረት እስራኤል የተረፋቸውን የበጉን ሥጋ በእሳት ውስጥ ጨምረውታል፡፡ በቤተክርስቲያናችንም ይህን መሰረት በማድረግ መሥዋዕት አያድርም በማለት ከላይ በተገለጠው መሠረት ሥርዓት ደንግጋለች የበጉን ጥብስ ሥጋ ሲበሉ ጫማቸውን ተጫምተው ወገባቸውን ታጥቀው ኮፍያቸውን ደፍተው በትራቸውን ይዘው እየተቻኮሉ እንዲበሉ ታዘው ነበር፡፡ ይህም ዛሬ ላለነው ክርስቲያኖች ምሳሌ ሆነን የአማናዊን በግ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋውንና ደሙን ስንቀበል ምግባረ ወንጌል ሰርተን (ወንጌል ተጫምተን)፣ የንጽህናን ዝናር በወገባችን ታጥቀን፣ አክሊለ

ሦክን ነገረ መስቀሉን እያዘከርን ሞት እንዳለብን ለማሰብ ሳይቀድመን እና ፈጥነን ንስሐ በመግባት መሆን እንዳለበት ያስረዳናል። የበጉን አጥንት እንዳይሰብሩ ማስጠንቀቂያ መስጠቱ የአማናዊው በግ የኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌው በመሆኑ ሲሆን ከጌታ ግራና ቀኝ የተሰቀሉት ወንበዴዎች ጭናቸውን ሲሰብሩ የጌታን ግን አልነኩም ነበር። ይህም የሆነው ትንቢቱ እንዲፈጸም ነው። *ዘጸ12÷6ዮሐ* 19÷36

የምስጢረ ቁርባን አመሰራረት

ምስጢረ ቁርባን የተመሠረተው በራሱ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ጌታ በጸሎተ ሐሙስ የደቀ መዛሙርቱን እግር ካጠበ በኋላ እንጀራም አንስቶ ባርኮ ቆርሶም ለደቀመዛሙርቱ ሰጠና እንካችሁ ብሉ ይህ ስጋዬ ነው አለ። ጽዋውንም አንስቶ አመስግኖ ሰጣቸው እንዲህም አለ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው። *ማቴ26÷26-29* ባለ ጊዜ ምስጢረ ቁርባን ተመሠረተ። ስለብዙዎች የኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው ማለቱም ስጋ ወደሙ አንድ ጊዜ ተመስርቶ እስከ ዕለተ ምጽአት ሲሰጥ መኖሩን ያሳያል። ‹‹ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህ አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጓልና›› *ዕብ 7÷27*

ስንዴና ወይን

ቤተክርስቲያን የጌታን ቅዱስ ስጋ ክቡር ደም ከወይንና ከስንዴ ታዘጋጃለች። ይህ የሆነበት ምክንያት የመጀመሪያው ጌታችን ለደቀመዛሙርቱ ስጋውና ደሙን ለወይንና በስንዴ ስለሰጠ ነው። *ማቴ26÷29* ቤተክርስቲያን ይህን አብነት በማድረግ ጎብስቱ (ስንዴው) በወራት ከደረሰ ዋግ ካልመታውና እንክርዳድ ከሌለበት (የተለቀመ) ንፁሕ ስንዴ ታዘጋጃለች። በተጨማሪ ጎብስቱ ነቅዕ የሌለበትና ያላፈራ ያልጠቆረ መሆን ይኖርበታል። በዚህ ጊዜ ለመሥዋዕት የተገባ ይሆናል ደሙን ደግሞ ከወይን የምታዘጋጅ ሲሆን ወይኑ ለመሥዋዕት የተገባ ይሆን ዘንድ ወፍያልመጠጠው ይሆናል ያልቆረጠው መጀመሪያ የደረሰው መሆን አለበት። ጌታ በወይን በስንዴ ያቀረበበት ምክንያት

1. ምሳሌውን እውን ለማድረግ ነው፡- እስራኤላውያን በበረሃ ሲጓዙ በረሃብ እንዳይሞቱ ሙሴ ጸልዮ ከሰማይ መና ወርዶላቸው ተመግበዋል ይህ ምሳሌ ነው። የክርስቶስን ስጋና ደም በልተን ከሞተነፍስ እንደምንድን የሚያጠይቅ ነው። ከሰማይ የወረደውን መና (ጎብስት) ተመግበው ንግስት አርያም ከሆነች ከእመቤታችን የተወለደውን የክርስቶስን ቅዱስ ስጋና ክቡር ደም ተቀብለን ከዘላለማዊ ሞት እንድናለን ይህ የክርስቶስ ስጋና ደም የሚዘጋጀውም ከጎብስትና ከወይን ነው። ስለዚህ ጌታ ሲናገር ‹‹የህይወት እንጀራ እኔ ነኝ። አባቶቻችሁ በምድረበዳ መና በሉ ሞቱም ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው። እኔም ስለ ዓለም ህይወት የምሰጠው ሥጋዬ ነው።›› ብሏል *ዮሐ6÷49-5*
2. ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ ፡- ትንቢቱ በመዝሙረኛው የተነገረው ‹‹በልቤ ደስታን ጨምረህ ከስንዴ ፍሬና ከወይ ከዘይትም ይልቅ በዛ›› *መዝ 4÷7* በማለት በሥጋወደሙና በህይማኖ ስለምናገኘው ደገወሐሴት ትንቢት ተናገረ። ዘይት ተስፋ ህይማኖትን ያመለክታል።
3. በምናውቀው ማድረጉ ነው፡- ጎብስትና ወይን ለሰው ልጅ እጅግ የሚጠቅሙ ለጤንነት የሚስማሙ ገንቢ የሆኑ የእህልና የፍራፍሬ ዘሮች ናቸው የሰው ልጅ በዕለት ተዕለት ኑሮው እነዚህን ምግቦች ስለሚጠቀምባቸው ያውቋቸዋል በቀላሉም ሊገኙ የሚችሉ ናቸው።

ጌታ ቅዱስ ቁርባንን በመብልና በመጠጥ ለምን አደረገ

ጌታም ለሰው የሚስማማን፤ የሰው ጎሊና የማይጨነቅበትን ያውቃልና በምናውቀው ስንዴና ወይን የዘላለምን ሕይወት እንድናገኝ አድርጓል ።

- ስንዴ ስብ ሥጋን ይመስላል ወይን ደግሞ ትኩስ ደምን ይመስላልና ስለዚህ በሚመስል ነገር መስጠቱ ነው።
- መብል መጠጥ ያፋቅራል። ጌታም ፍጹም እዳፈቀረን ለሚጠይቅ (ለማስረዳት) ቅዱስ ስጋውን ክቡር ደሙን ለመብልና ለመጠጥ አደረገልን

- መብልና መጠጥ ከሰውነት ይዋሐዳል። ጌታም ፍጹም ተዋህዶን እንደሚኖር ሲያጠይቅ በመብልና በመጠጥ አደረገልን

የምስጢረ ቁርባን አቀራረብ

ይህ የሐዲስ ኪዳን መስዋዕት ለሐዲስ ኪዳን የክህነት አገልግሎት በተሾሙ ሐዋርያት ይቀርብ ነበር። ሐዋርያትም በሲኖዶሳቸው ሌሎች ካህናትን ይሾሙ ስለነበር አገልግሎቱ ዕለት ዕለት በሁሉም ቦታ ይፈጸም ነበር። ምእመናንም የቁርባንን ምስጢር በማወቅ ስለኃጢአታቸው ንስሐ ገብተውና ተዘጋጅተው ይቀበሉ ነበር። አንዳንዶች የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ባለመረዳት ጎብስቱንና ወይኑን እንደማንኛውም ምግብ ይበሉና ይጠጡ ስለነበር ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ በማለት ገሥጾአቸዋል። ‹‹የምትበሉባቸውና የምትጠጡባቸው ቤቶች የሏችሁምን፣ ወይስ የእግዚአብሔርን ማኅበር ትንቃላችሁን? ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ደም የጠጣሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት። ሰው ግን ራሱን ይፈትን እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ። ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ስጋና ደም ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና። *1ቆሮ 11÷ 23-32* ከሐዋርያት ዘመን ጀምሮ ቤተክርስቲያን ባሳለፈቻቸው ረጅም አመታት የተነሱ ቅዱሳን አበውና ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ስለምስጢረ ቁርባን አቀራረብ ሥርዓት ሰርተዋል። የመጀመሪያው ሥርዓት የጌታ ቅዱስ ስጋና ክቡር ደም የሚቀመጥበት /የሚሰዋበት/ መሰዊያውን ማዘጋጀት ነው። በቤተክርስቲያናችን የቅዱስ ስጋውና የክቡር ደሙ ማክበሪያ ታቦት ነው። እግዚአብሔር ጥንትም ሆነ አሁን ወደፊትም የማይለወጥ ስለሆነ ቅዱሳን አባቶችን የብሉይ ኪዳንን ታቦት በሐዲስ ሥርዓት በሐዲስ ኪዳን አገልግሎት አውለውታል።

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ጎብስቱ ተለውጦ የጌታ ቅዱስ ሥጋ ወይኑ ተለውጦ የጌታ ክቡር ደም የሚሆንበትም ምስጢር የሚፈፀመው ለዚህ አገልግሎት ተብሎ በጌታና በቅዱሳን አበው በተደረሰ ቅዳሴ ጸሎት ነው። ጸሎቱ ምንጊዜም ቢሆን የሚደርሰው በቤተክርስቲያን አባቶች በካህና አማካይነት ነው። መብራት ይበራል፣ እጣን ይታጠናል ጸሎት ቅዳሴው በካህናቱ በህዝቡ መካከል በመቀባበል በዜማ ይጸለያል። ምእመናን በክርስቶስ ደም ይነጻሉ ሲባል ከዘመናት በፊት በተፈጸመው በክርስቶስ መሥዋዕትነት መሆኑ ቢታወቅም ታሪኩን በመስማት ብቻ አይደለም። በተግባር አሁንም የዚያን ወቅት ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም በየዕለቱ የቀራንዮ ምሳሌ ከሆነችው ከቅድስት ቤተክርስቲያን ያገኙታል። ቅዱስ ስጋውንም ይበላሉ ክቡር ደሙንም ይጠጣሉ።

የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም በመቀበል የሚገኘው ጥቅም

1. **ክርስቶስ ከእኛ ውስጥ ይኖራል፦** ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ውስጥ የሚኖረው እኛም በእርሱ የምንኖረው ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ስንቀበል ነው። ‹‹ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ›› ብሏልና *ዮሐ6÷56*
2. **ኃጢአታችን ይሰረይልናል፦** የቆሸሸን ልብስ ውሃን ሳሙና እንደማያነጹት በኃጢአት የጎሰቆለው ሰውነታችን በንስሐ ጸንቶ የክርስቶስን ሥጋና ደም በመቀበል ከኃጢአት የምንነጻ መሆኑን ጌታ ‹‹ስለብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው›› በማለት ተናግሯል። *ማቴ26÷27*
3. **የነፍስና የሥጋ በረከት እናገኛለን፦** ፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ‹‹የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም። በእኔ የሚያምን ሁልጊዜ አይጠማም።›› *ዮሐ6÷35* በማለት የነፍስ የሥጋ በረከት እንደምናገኝ ረቂብና ጥም እንደማይገጥመን፣ በመንፈሳዊ ሕይወትና እውቀት የምንበለጽግበት ታላቅ ምስጢር መሆኑን ተናግሯል።
4. **የክርስቶስን መከራ ያሳስበናል፦** ‹‹ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪሚጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና›› *1ቆሮ 11÷26* በማለት ቅዱስ ጳውሎስ አስረድቷል።
5. **የዘላለም ሕይወትን እናገኛለን፦** ‹‹ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው እናም በመጨረሻ ቀን አስነሳዋለሁ።›› *ዮሐ6÷54* በማለት ጌታችን ራሱ የዘላለም ሕይወት የምናገኘው ስጋና ደሙን ካልተቀበልን ግን ሕይወት እንደሌለንም ሲጠይቅ ‹‹እውነት እውነት

እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም›› ብሏል *ዮሐ6÷53*

- የክርስቶስ ሥጋና ደም በመቀበላችን ሁላችን አንድ አካል፣ አንድ ሐሳብ፣ አንድ አላማ ይኖረናል፡፡ “አንድ እንጀራ ስለሆነ እኛ ብዙዎች ስንሆን አንድ ሥጋ ነን ያን አንዱን እንጀራ እንካፈላለንና›› ብሏል *1ቆሮ 10÷17*

የጌታ ሥጋና ደሙ መታሰቢያ ወይስ አማናዊ የመናፍቁ አለም ቅዱስ ቁርባንን በተመለከተ የተሳሳተ አመለካከትና እምነት ያራምዳል፡፡ ለዚሁም ‹‹ስለእናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው ይህን ለመታሰቢያ አድርጉት አለ›› *ሉቃ22÷19* የሚለውን የጌታን አነጋገርን አስረጅ አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ፡፡ ዳሩ ግን ይህ የጌታ አነጋገር እነሱ በተረዱትና በተረጎሙት መልኩ እንዳልሆነ የራሱ የጌታችንን ቃል አስረጅ አድርገን ማቅረብ እንችላለን፡፡

‹‹እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ፤ ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ ሁላች ከእርሱ ጠጡ ስለብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው፡፡›› *ማቴ26÷26-28*

ከላይ በግልጽ እንደተመለከተው ጌታ ኅብስቱን አንሥቶ የሥጋው ምሳሌ ወይም መታሰቢያ እንዳልሆነ አማናዊ ሥጋው እንደሆነ ገልጾአል በጽዋ ያለውንም ወይን ይህ ደሜ ነው አለ አንጂ የደሜ ምሳሌ ወይም መታሰቢያ ነው አላለም፡፡ እንዲሁም ‹‹ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ. . . ›› *ዮሐ6÷54* በማለት ሥጋወደሙ አማናዊ መሆኑን እንጂ ምሳሌ ወይም መታሰቢያ አለመሆኑን አስገንዝቦናል፡፡ ይህ እንዲህ ከሆነ ‹‹ለመታሰቢያዬ አድርጉ ሲል ሥጋውን በበላን ደሙን በጠጣን ጊዜ ስለእኛ ሲል መከራ የተቀበለውን የተሰቀለውን እርሱን እናስባለን፡፡ በቤተልሔም ዋሻ እስከ ቀራንዮ ኮረብታ ለሰው ልጆች ጽናትና የፈጸመውን የማዳን ሥራ እንድናዘክር የሚያስገነዝብ አነጋገር እንጂ የሥጋ ወደሙን አማናዊነት የሚያስተባብል አይደለም፡፡

ምዕራፍ ስድስት
ምስጢረ ትንሳኤ ሙታን

ትርጓሜ

- ✓ ትንሳኤ የሚለው ቃል ተንስእ ከሚለው የግእዝ ግስ የተገኘ ቃል ሲሆን መነሳት ማለት ነው። ይህም መነሳት የስጋ ነው ምክንያቱም ነፍስ በባሕርይዋ የማትሞት የማትፈርስና የማትበሰብስ ናት። ስለዚህ ትንሳኤ የሚሆነው ሥጋ ሞቶ ፈርሶና በስብሶ ይኖር ከነበረበት ከመቃብር በሥልጣነ እግዚአብሔር ተነሥቶ ከነፍስ ጋር በመዋሐድ ነው።
- ✓ ትንሳኤ የሙታን እንደገና በሥጋ መነሣት ነው። ሕያዊት ነፍስ ያላቸው ሰዎች በሥጋ ከሞቱ በኋላ ተለያይተው የነበሩት ነፍስና ሥጋ ተዋህደው የሚነሱበት ታላቅ ምስጢር ነው። ከሃያሁለቱ ፍጥረታት መካከል ትንሳኤ ያለው የሰው ልጅ ብቻ ነው። ሌሎች ፍጥረታት ነፍሳቸው ደማዊት በመሆኗ ፈርሰው በስብሰው የሚቀሩ ናቸው። የሰው ልጅ ከሞት በኋላ በነፍስና በሥጋ ሕይወት ስለሚያገኝ ከእንስሳት ይለያል።

  ፍጥረታዊው ሰው ጊዜው ሲደርስ የሚሞት መሆኑ ማለትም ነፍስና ሥጋው እንደሚለያዩ ቀደም ተብሎ ተገልያአል። ይሁን እንጂ እነዚህ የተለያዩት ስጋና ነፍስ በመጨረሻው ዘመን እንደገና ተዋህዶ እንዲኖራቸው ዳግመኛ በማይፈርስና በማይበሰብስ ስጋ እንደሚነሱ የሚገልፀውየቤተክርስቲያን እምነትና ትምህርት ምስጢረ ትንሳኤ ሙንታ ይባላል። ይህም ትምህርት ለሰው አስተሳሰብ ረቂቅ ምስጢር በመሆኑ ምስጢረ ትንሳኤ ሙታን ተብሏል።

አስፈላጊነት

ለሰው ትንሳኤ ያስፈለገበት ምክንያት ሰው የተፈጠረው ነፍሱና ሥጋው ሳይለያይ በሕይወት ለመኖር እንጂ ለሞት አልነበረም። ነገር ግን በኃጢአት ምክንያት በራሱ ላይ ሞቱን በማምጣቱ ሞት የማይገባው አምላክ ሞቶ ከኃጢአት ፍርድ በማዳን ሞትን በማጥፋት በቀደመው ሕይወቱ እንዲኖር ለሰው ልጅ ትንሳኤው ሰጠው።

ስለ ትንሳኤ ሙታን የተነገሩ ትንቢቶች እና ምሳሌዎች

በብሉይ ኪዳን

ምስጢረ ትንሳኤ ሙታን ቀደም ብሎ በነቢያት ታውቆ ስለነበር ስለ ትንሳኤ ሙታን ብዙ የተነገሩ ትንቢቶች አሉ።

- ✓ አባታችን ኢዮብ በሙታን መነሳት ላይ ያለውን ተስፋ በሚያመለክት አነጋገር «እኔ ግን የሚቤዠኝ ሕያው እንደሆነ፣ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም፣ ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ፣ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ እና እኔ እራሴ አየዋለሁ፣ አይኖቼም ይመለከቱታል ከእኔም ሌላ አይደለም ልቤ በመናፈቅ ዝሏል» *ኢዮ19÷25-27* በማለት በትንሳኤ ጌታን ማየት እንደሚናፍቅ ተናገረ።
- ✓ ነብዩ ዳዊትም ስለትንሳኤ ሲናገር «ሥጋዬ ደግሞ በተስፋ ታድራለች ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም» *መዝ 15(16)÷9-10* በማለት ለጊዜው ስለራሱ ፍጻሜው ግን ስለጌታችን ትንሳኤ ተናገረ።

- ✓ ነቢዩ ሕዝቅኤል ትንሳኤን በተመለከተ «ጌታ እግዚአብሔር ለእነዚህ አጥንቶች እንዲህ ይላል፡፡ እነሆ ትንፋሽን አገባባችኋለሁ በሕይወትም ትኖራላችሁ» *ሕዝ37÷5* በማለት ተናግሯል፡፡
- ✓ ነቢዩ ኢሳያስ «ሙታንህ ሕያዋን ይሆናሉ ሬሳዎችም ይነሳሉ በምድርም የምትኖር ሆይ ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና ምድርም ሙታንን ታወጣለችና ንቁ ዘምሩም» *ኢሳ 26÷19* በማለት ስለ ትንሳኤ ትንቢት ተናገረ፡፡

በሐዲስ ኪዳን

- ✓ ክብር ምስጋና ለእርሱ ይሁንና ጌታችን የሙታንን ትንሳኤ አስመልክቶ ሲናገር «በመቃብር ያሉ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል መልካምምያደረጉለህይወት ትንሣኤ ክፉምያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ፡፡» ብሏል *ዮሐ5÷28-29*
- ✓ በትንሳኤ ሙታን ለማያምኑሰዱቃውያን በሰጠው መልስ «መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁበትንሣኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእክት በሰማይ ይሆና እንጂ አያገቡም አይጋቡም ስለትንሣኤ ሙታንግን እኔ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅ አምላክ የያዕቆብ አምላክ ነኝየሚል ከእግዚአብሔር ዘንድ ወደ እናንተ የተባለውን አላነበባችሁምን? የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም» ብሎአል *ማቴ 22÷29-32*
- ✓ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ትንሳኤ ሙታንን አስመልክቶ ሲመሰክር «እነዚህም እራሳቸው ደግሞ የሚጠብቁት ጻድቃንም አመፀኞችም ከሙታን ይነሱ ዘንድ እንዳላቸው ተስፋ በእግዚአብሔር ዘንድ አለኝ» ብሏል *የሐዋ 24÷15*
- ✓ ቅዱስ ጳውሎስ በእምነት ለሚመስሉት ክርስቲያኖች ሲያስተምር «ክርስቶስ ከሞት እንደተነሳ የሚሰበክ ከሆነ እንዴት ከእናንተ አንዳንዶቹ የሙታን ትንሳኤ የለም ይላሉ ሙታን ከሞት የማይነሱ ከሆነ ክርስቶስም አልተነሳማ ክርስቶስ ካልተነሳ ደግሞ የእኛ ትምህርት ሆነ የእናንተም እምነት ከንቱ መሆኑ ነው፡፡» *1ቆሮ 15÷12-141ቆሮ 15÷35-37 እና 1ቆሮ15÷51-52* ስለሙታን አነሳስ እና ስለትንሳኤ ሙታን ረቂቅ ምስጢርነት አያይዞ ተናግሯል፡፡

የምስጢረ ትንሳኤ ሙታን ምሳሌ

- ✓ በአቤል ሞት ሞታችን፣ በሄኖክ ዕርገት ትንሣኤያችን ታውቋል፡፡ ***ዘፍ 4÷8 ፣ ዘፍ 5÷24***
- ✓ አቤል ከሞተ በኋላ ደሙ መናገሩ፡፡ ***ዘፍ 4÷10***
- ✓ ኖኅ በጥፋት ውሃ ጊዜ ወደ መርከብ መግባቱ ለመቀበራችን፣ መውጣቱ ለመነሳታችን ምሳሌነው፡፡ ***ዘፍ 6÷7-8***
- ✓ አብርሃምና ሣራ ካረጁ በኋላ ሙቀትና ልምላሜ አግኝተው ይስሐቅን ወልደዋል፡፡ ማርጀታቸው ለመሞታችን፣ ሙቀት ማግኘታቸው ነፋስ ቃል አእምሮ አግኝተን ለመነሳታችን ምሳሌ ነው፡፡ ***ዘፍ 21÷1-2***
- ✓ ይስሐቅ አባቱ በሕሊናው ከሰዋው በኋላ ከሞት መዳኑ የትንሳኤ ምሳሌ ነው***ዘፍ 22***
- ✓ ያዕቆብና ዮሴፍ በሞቱ ጊዜ አጥንታቸውን ከግብፅ ወደ ከነዓን እንደወጣ ተናግረዋል፡፡ ግብፅ የመቃብር ከነዓን የመንግስተ ሳያት ምሳሌ ናት፡፡ ዮሴፍና ያዕቆብ አውጡት ማለታቸው ትንሳኤ ሙታንን ለመግለፅ ሲሉ ነው፡፡ ***ዘፍ47÷29-31 ዘፍ50÷24***

የትንሳኤ አይነቶች

የትንሳዔ አይነቶቸ ሁለት ሲሆኑ እነሱም፡-

1ትንሳኤ ዘለክብር(የክብር ትንሣኤ)
2ትንሳኤ ዘለኃሳር

«በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሳኤ ይወጣሉና በዚህ አታድንቁ።» *ዮሐ5÷29* በማለት ሙታን ከትንሣኤ በኋላ ምን እንደሚጠብቃቸው ያሳያል። በዚህ አባባል ክፉ አድራጊዎች የክፉ ስራቸውን ውጤት የዘለዓም ቅጣት ፍርድ እንደሚቀበሉና ትንሳኤአቸው ለውርደትና ለጉስቁልና እንደሆነ በጎ አድራጊዎች ደግሞ ትንሳኤአቸው ለክብር እንደሆነ በግልጽ አስረድቷል።

«የዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል ከመንግስቱም እንቅፋትን ሁሉ አመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ ወደ እቶነ እሳትም ይጥሏቸዋል። በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።» *ማቴ13÷41-43፤ 49-50*ማለት ወንጌላዊው ከትንሣኤ በኋላ በዓለም ሳለ በሰሩት ስራ የሚፈረድ መሆኑን በእምነት ብቻ ከመልካም ሥነ ምግባር ተገልሎ በመኖር ህይወት የማይገኝ መሆኑን በግልፅ መስክሮአል። ቅዱስ ማርቆስም ይህንኑ ከትንሳኤ በኋላ በሙታን ላይ እንደየሥራቸው ከአምላክ የሚሰጠው ፍርድ *ማር 9÷46-48*ከአሰፈረው ቃል በዝርዝር ገልፆ ጽፎአል። *ማቴ 24÷15፣25 ፣ 16÷17*

ቅዱሳን መጻሕፍት እንደሚያስረዱን ጻድቃን «**የአባቴ ቡሩካን . . . መንግስትን ውረሱ**» በማለት ጌታ ሲናገር በዚህ ምድር የደረሰባቸውን መከራና ያዘኑትን እጥፍ ደስታ ይደሰታሉ።

ኃጥአንን «እናንት ርጉማን ወደ ዘላለም እሳት ሂዱ» በማለት ጌታ ሲናገር ያንጊዜ ኃጥአን ያለቅሳሉ እንባቸው እንደክረምት ዝናብ ይወርዳል።

ቅዱስ ያዕቆብ ዘሥሩግ በቅዳሴው«ያን ጊዜ ለቅሶ ይሆናል የማይጠቅም ለቅሶ ያን ጊዜ ጩኸት ይሆል የማይጠቅም ጩኸት ነው። ያን ጊዜ ጥርስ ማፋጨት ይሆል» በማት ስለማይጠቅመውኃዘንና ለቅሶ ተናግሯል በሚጠቅመው ለቅሶ በዚህ ምድር ሳለን ኃጢአታችንን እያሰብን የምናለቅሰው ነው ለእውነት እግዚአብሔር በከሀሊነቱና በቸርነቱ ከዚህ ሞት ይሰውረን፤ እያሳየን ይልቀንም ክብሩን ያውርሰን እንጂ።

የጌታችን ትንሳኤ

አምላካችን ኢየሱስክርስቶስ ለሰው ልጅ ድኅነት መከራ ተቀብሎ እንደሚሞትና በሦተኛው ቀን እንደሚነሳ አስቀድሞ በነቢያት ትንቢት ተናግሯል *በመዝ 77 (78) ÷65* ላይ «እግዚአብሔርም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሳ የወይን ስካር እንደተወው እንደኃያልም ሰው፤ ጠላቶቹንም በኋላቸው መታ» በማለት በሰው ላይ ሰልጥኖ የነበረውን የሞት አገዛዝ ደምስሶ እንደተነሳ ከረጅም ዘመናት በኋላ የተፈጸመውን ድርጊት ተናግሯል።

ጌታችን ኢየሱስክርስቶስ ስለስቅለቱና ስለትንሳኤው ለሐዋርያት አስቀድሞ ነግሯቸዋል።«የሰው ልጅ በሰዎች እጅ አልፎ ይሰጣል፤ ይገድሉትማል ተገድሎም በሦስተኛው ቀን ይነሳል» ይላቸው ነበር *ማር 8÷31 ፣ ማቴ16÷21*ትንቢቱ እውን ይሆን ዘንድ ቀረበ፣ በሞቱ ሞታችንን የሚያጠፋ እርሱ ነው። ለሰው ልጆች ድኅነት ራሱን አሳልፎ ሊሰጥ ወዶአልና። «ነፍሴንም ስለበጎች አኖራለው . . . እኔ በፈቃዴ አኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወስዳት። ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሳት ሥልጣን አለንኝ *ዮሐ 10÷15 ና 18*

ጌታም በፈቃዱ ራሱን አሳልፎ ለአይሁድ ሰጠ *ዮሐ18÷4-12* የሰውን ልጅ ከሞትና ከግዞት ለማዳን አስራሦስቱን ሕማማተ መስቀል ተቀበለ። ሞተ ተቀበረ በሥጋው ወደመቃብር ወርዶ ፈርሶ በስብሶ መቅረትን አስወገደ፤ በነፍሱም ወደ ሲኦል በመውረድ ነፍሳትን ነፃ አወጣ። በትንቢትና በምሳሌ እንደተናገረውም በስጋው ወደ መቃብር ወርዶ ሦስት መዓልትና ሶስት ሌሊት ካደረ በኋላ በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ ስለትንሳኤውም መላእክቱ ለሐዋርያት «ሕያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጋላችሁ ተነሥቷል እንጂ በዚህ የለም።» ብለው አበሰሯቸው*ሉቃ 24÷5*ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ የተነሳው የመቃብሩን በር ሳይከፍት (በጎቱም መቃብር) ነው።

የጌታ መልአክ ለትንሳኤው ምስክር ይሆን ዘንድ ከሰማይ ወርዶ የመቃብሩን ድንጋይ አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ። «እነሆም የጌታ መልአክ ከሰማይ ስለወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ። ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ ተቀመጠ። መልአኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደበረዶ ነጭ ነበር።» የመቃብሩ ጠባቂዎች እርሱን ፈርተው ተፈነጋገሉ፤ ወደቁ። «ጠባቂዎቹም እርሱን ከመፍራት የተነሳ ተናወጡ እንደሞቱም ሆኑ፤ መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው እናንተ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹአውቃለሁና እንደተናገረ ተነሥቷል።» *ማቴ28÷1-10*አላቸው አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ በትንሳኤው እኛም ትንሳኤ እንዳለን አብስሮናል። እርሱ የትንሳኤያችን በኩር ነው። ቅዱስ ጳውሎስም «አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆነ ከሙታን ተነስቶአል ሞት ሰው በኩል ስለመጣ ትንሳኤ ሙታንም በሰው በኩል ሆኗል። «ሲል አስረድቷል *1ቆሮ 15÷20-22፣ ቆላ 1÷18*

«ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሞተና እንደተነሳ ካመንን እንዲሁም በኢየሱስ ክርስቶስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና» *1ተሰ 4÷14*

የጌታችን ትንሣኤ በራሱ ፈቃድ እና በገዛ ሥልጣኑበመሆኑ እንዲሁም ከተነሳ በኋላ ደግሞ ሞት ስለሌበት በእርሱ ፈቃድ ከሞት ከተነሱ ሰዎች ትንሳኤ ይለያል።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጅ ለማዳን በሥጋ ተገልጦ በዚህ ምድር ታይቷል። የማዳን ስራውን ፈፅሞ በክብር ዐርጓል። *ሉቃ 24÷49*

የጌታችን ዳግም ምፅአት

ጌታችን ወደዚህ ምድር ዳግም በተዋህደው ሥጋ ይመጣል። «እናንተ የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣ።» *የሐዋ 1÷11* ቅዱስን መላእክት አጅበውት በታላቅ ግርማ ነው። ነቢዩ ዘካርያስ«አምላኬ እግዚአብሔርም ከቅዱሳኑ ጋር ይመጣል።» ሲል ተናግሯል *ዘካ14÷6*

«የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና» *ማቴ 16÷27* «እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል አምላካችን ይመጣል ዝምም አይልም እሳት በፊቱ ይቃጠላል» *መዝ49÷2*«እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል፣ ዐይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ።» *ራዕ 1÷7*

የሚመጣው መቼ ነው?

የጌታችን መምጣት ማንም አያውቀውም የሚመጣበት ቀን አይታወቅም፤ መምጣቱም እንደ ድንገት ነው። ራሱ ጌታ «ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ግን የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን

ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም» *ማር 13÷32*ማለት ከእግዚአብሔር በቀር ሰው የማያውቀው መሆን ተናግሯል፡፡

የሚመጣው ለምንድን ነው?

ጌታችን ወዲዚህ ምድር ዳግመኛ የሚመጣው ለሰው ልጅ ሁሉ እንደየስራው ዋጋውን ሊሰጥ ነው፡፡ ነቢዩ እግዚአብሔር ኢሳያስ «እነሆ ጌታ እግዚአብሄር እንደኃያል ይመጣል ክንድም ስለ እርሱ ይገዛል እነሆነ ዋጋው ከእርሱ ጋር ደመወዝም በፊቱ ነው፡፡» *ኢሳ 40÷10*ማለት የተናገረውን ጌታ ራሱ*በራዕ22÷12* ላይ «እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው መጠን እከፍለው ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ፡፡» ብሏል

የሙታን አነሳስ

«በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምጽ ያልፋሉ የሰማይ ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል ምድርም በእርስዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል» *2ጴጥ 3÷10፡*ጳሞትህ ተነሳ የሚል አዋጅ በቅዱስ ሚካኤል ይታወጃል፤ ሦስት ረቂቃን ነጋሪቶች ይጎሰማሉ፡፡ ይህም የጌታ ትዕዛዝ ነው፡፡ «ጌታ እራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና እንደተባለ»*1ተሰ4÷16*

- የመጀመሪያው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አውሬ የበላው ነፋስ የበተነው ያለቀው የደቀቀው ሁሉ የራሱ ቅል በፈረሰበት ቦታ ላይ ይሰበሰባል ***ያዕቆብ ዘሥሩግ ቁ91***
- ሁለተኛ ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አጥንትና ሥጋ ተዋሕደው ሳይንቀሳቀስ ትኩስ ሬሳ ይሆናል፡፡ አጥንቶችና ጅማቶች ከሥጋና ከደም ጋር ይያያዛሉ እስኪነሱ ያለመንቀሳቀስ ፍፁም በድን ይሆናሉ፡፡
- ሦስተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ በቀዳሚ አካል ለምትናገር አንደበት ከራስ ጠጉራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው ከቁጥር ሳይጎድሉ ከሰውነታቸው ሳይከፈሉ ወንድ በአቅመ አዳም የሰላሳ ዓመት ጎልማሳ ሆነው ሴት በአቅመ ሄዋን የአስራ አምስት አመት ሆነው በዓርባ ቀን በእናቱ ማህፀን ደም ሆኖ የወረደ ጽንስ ሳይቀር በጎም ይሁን ክፉ ስራቸውን ይዘው ይነሳሉ ጌታ ራሱ በማቴዎስ ወንጌል ላይ እንደተናገረው በጎቹን በቀኝ ፍየሎቹን በግራ ያቆማል *ማቴ 25÷31-46*

ጻድቃን በበግ ኃጥአን በፍየል የተመሰሉት ለምንድን ነው?

የበጎች ተፈጥሮ ከጻድቃን ጋር የፍየሎች ተፈጥሮ ከኃጥአን ጋር ይመሳሳሉ፡፡

- ከበጎች መካከል አንዲቱን ተኩላ ቢነጥቃቸው በረው ወደዱር ይገባሉ ወደዚያ ቦታ ተመልሰው አይሄዱም፡፡ ጻድቃንም ከሰው መካከል አንዱ በሞት ቢነጠቅ ይሄ እጣ ነገ ለእኔም ይደርሳል ብለው ከኃጢአት ርቀው እግዚአብሔርን በንጽሕና ያገለግሉታል እንጂ ዳግሞ ወደዚያ ኃጢአት አይመለሱም
- ፍየሎች ግን ከመካከላቸው አንዲቱን ተኩላ ቢነጥቅባቸው ለጊዜው ከዚያ ቦታ ይሸሻሉና ተመልሰው እዚያ ቦታ ይገኛሉ፡፡ ኃጥአንም ከመካከላቸው አንዱ ቢሞት ለጊዜው ደንግጠው ከኃጢአት ቢርቁም ኋላ ወደጥፋታቸው ይመለሳሉና በፍየል መሰላቸው፡፡
- በግ ኃፍረታን አታሳይም በላቷ ትሸፍነዋለች ጻድቃንም ኃጥያት ቢሰሩ እንኳ ኃጢአታቸውን በንስሐ ይሸፍናሉ

- ፍየሏ ኃፍረቷ የተገለጠ ነው፤ ላቷም የተሰቀለ ነው። ኃጥአንም ኃጢአት ቢሠሩ በንስሐ እናጥፋው አይሉም እንደውም ኃጢአታቸው በሰው ሁሉ ፊት የተገለጠ ነው።
- በግ ያለችበትን ቦታ የዋለችበትን አይታወቅም ጻድቃንም በትህትናቸው በዝምታቸው ያሉበት ቦታ አይታወቅም

የግራና የቀኝ ምሳሌ

- ቀኝ ቀና፣ ፈጣን እና ብርቱ ነው። ጻድቃንም ሃይማኖት ምግባር ለመስራት ቀና፣ ፈጣንና ብርቱዎች ናቸው። ጻድቃን በቀኝ የሚቆሙት ምሳሌያቸው ስለሆነ ነው
- ኃጥአን በግራ የሚቆሙት ምሳሌአቸው ስለሆነ ነው። ግራ ጠማማ፣ ዳተኛ እና ስነፍ ነው። ኃጥአንም ሃይማኖት ምግባር ለመስራት ጠማማ፣ ዳተኛ እና ሰነፍ በመሆናቸው ነው።

ገነት ሲኦል መንግስተ ሰማያት እና ገሀነመ እሳት

እስከ እለተ ምፅት ድረስ ነፍሳት ጊዜያዊ ማረፊያ ቦታ አላቸው። ገነትና ሲኦል ይባላሉ። እነዚህ የሚያልፉ ናቸው እስከምፅአት መልካም የሰሩ፣ ሰውነታቸውን እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ መሥዋዕት ያደረጉ ጻድቃን በገነት የሚያርፉ ይሆናሉ።

ኃጥአንም የእግዚአብሔርን ሕግና ትእዛዝ የጣሱ በበደል ለሥጋቸው ምኞት፣ ለሆዳቸው መሙላት፣ ለፊታቸው መቅላት ብቻ ሲጨነቁ የነፍሳቸውን ነገር የተው ሰዎች የሚቀጡበት ጊዜያዊ ማረፊያ ሲኦል ይባላል።

ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ተብላ የምትጠራው አራተኛዋ ሰማይ፤ በሰው ህሊና ያልታሰበች እግዚአብሔርም ለወዳጆቹ (ሕጉን ለጠበቁ) የዘላለም ሕይወት ያገኙበት ዘንድ ያዘጋጃት ሥፍራ መንግስተ ሰማይ ናት።

እግዚአብሔር ከእሳት ብርሃኑን ነስቶ ሰማያትን ፈጠረ በኋላ ፍፁም ብርሃን የሌለው የእሳቱን ዝቃጭ ከመሬት በታች አኑሮታል በርባኖስ የሚባልም ስያሜ አለው ከእግዚአብሔር ሕግና ትዕዛዝ አፈንግጠው በኃጢአት በክህደት የነበሩ ኃጥአን ከጊዜያዊ የቅጣት ቦታ ከሲኦል በመጨረሻው የፍርድ ጊዜ የሚዘዋወሩበት ቦታ ገሀነመ እሳት ትባላለች።

ዋቢ መጽሐፍት

- መጽሐፍ ቅዱስ
- አዕማደ ምሥጢር
- አምደ ሃይማኖት
- ነገረ ሃይማኖት
- የትምህርተ ሃይማኖት መግቢያ